# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 216 ሚያዝያ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የሥርዓተ ምግብና ኒውትሪሽን ሽግግር ፍኖተ ካርታ ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል

### -ግብርና ሚኒስቴር ሦስት ስትራቴጂዎችን ይፋ አደረገ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሥርዓተ ምግብና ኒውትሪሽን ሽግግር ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ እንደተገባ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። ሚኒስቴሩ ሦስት ስትራቴጂዎችን ይፋ አድርጓል።

የግብርና ሚኒስቴር ከክልል ግብርና እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮዎች እንዲሁም ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ብሔራዊ የምግብ ደህንነትና ጥራት ለተቀዳሚ የግብርና ምርቶች ስትራቴጂ፤ ብሔራዊ የድህረ ምርት አያያዝ ስትራቴጂ፤ ሥርዓተ ምግብ ተኮር የምግብ ሥርዓት ስትራቴጂ የተሰኙ ሦስት ስትራቴጂዎችን ትናንት ይፋ አድርጓል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሥርዓተ ምግብና ኒውትሪሽን ሽግግር ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። ይህ ፍኖተ ካርታ ከማሳ እስከ ማዕድ ያለውን ሰንሰለት መሠረት በማድረግ የሥርዓተ ምግብና የሥነ ምግብ ጉዳዮችን ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው።

ምግብ ማምረት አንድ ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ምርቱን በብዛትና በጥራት ማምረት እንዲሁም ብክነትን በመቀነስ የምግብ ደህንነትንና


የሥርዓተ ምግብና...ወደ ገጽ 4 ዞሯል










## “በኢ-መደበኛ ንግድ የተደራጀን የልማት ተነሺዎች መፍትሔ እንሻለን”

### - በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ በአልባሳት የተደራጁ ነጋዴዎች

## “በክፍለ ከተማው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ለከንቲባ ጽህፈት ቤት አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ”

### - ከተማ አስተዳደሩ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢ-መደበኛ ንግድ የተደራጀን የልማት ተነሺዎች መፍትሔ እንሻለን ሲሉ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ በአልባሳት የተደራጁ ነጋዴዎች ገለጹ። ከተማ አስተዳደሩ በበኩሉ በክፍለ ከተማው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ለከንቲባ ጽህፈት ቤት አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ ::


“በኢ-መደበኛ ንግድ የተደራጀን..ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## ኃይል ማመንጫ ጣቢያው ባከናወነው ጥገና 75 ሚሊዮን ብር ወጪ አድኗል



ኢንጂነር ሹመት በላቸው

**ኢያሱ መሰለ**

የም ዞን ፎፉ፡- የግልገል ጊቤ-2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የውስጥ አቅሙን ተጠቅሞ በሦስት ተርባይኖች ላይ ባደረገው ጥገና 75 ሚሊዮን ብር የሚገመት ወጪ ማዳኑን ገለጸ::

ኢንጂነር ሹመት በላቸው የግልገል ጊቤ-2 ኃይል ማመንጫ


ኃይል ማመንጫ ጣቢያው ..ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የአትክልትና የፍራፍሬ ምርታማነት መጨመር የዋጋ ንረቱን አረጋግቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአትክልትንና የፍራፍሬን ምርትና ምርታማነት በእጥፍ ለማሳደግ እየተሠራ ያለው ሥራ ውጤታማ በመሆኑ የዋጋ ንረቱ ተረጋግቷል ሲል ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ::

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአትክልትንና የፍራፍሬን ምርትና ምርታማነት በእጥፍ ለማሳደግ እየተሠራ ያለው ሥራ ውጤታማ ነው:: በአሁኑ ጊዜም የተትረፈረፈ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ለገበያ እየቀረበ ነው፤ ይህም የዋጋ ንረቱን ማረጋጋት ችሏል::

በ2016 ዓ.ም የበጋ መስኖ ልማት ሥራ የለሙ


የአትክልትና የፍራፍሬ ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ዜና

# በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛው የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ዝናብ ያገኛሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ አስር ቀናት በአብዛኞዎቹ የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንደገለጸው፤ በቀጣይ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኞዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረ ይሄዳል።

ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኞዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረ እንደሚሄድ በመግለጽ፤ የበልግ ዝናብ በደቡብ፣ደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖር በትንበያው ተገልጿል።

በበልግ አብቃይ አካባቢዎች በርካታ ቦታዎችን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣በደቡብና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ጠቁሟል።

ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ እንደሚሄድ የገለጸው፤ ትንበያው በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተጠቁሟል።

የአየር ሁኔታው የበልግ የግብርና ሥራን ለማከናወን፣የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና ቀደም ብለው ለዘሩ እንደሚረዳ በመግለጽ፤ በቡቃያ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ትንበያው ጠቁሟል።

በተለይም እርጥበታማ ሁኔታው ለእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታ መሆኑን ጠቅሶ፤ አርሶ አደሮች ግብዓቶችን በመጠቀም የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማካሄድ እንዳለባቸው አመላክቷል።

በሚቀጥሉት ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣አዋሽ፣ አባይ፣ገናሌ ዳዋ፣በመካከለኛው ተከዜ፣በላይኛው ዋቤ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው በመግለጽ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት ለገጸ ምድርም ሆነ ለከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መጎልበት አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል።

# ፍርድ ቤቱ የሕዝብ አመኔታ የተቸረው ተቋም እንዲሆን በቅንጅት መሥራት ይገባል

## - መዝገቦች በተቀመጠላቸው ጊዜ እልባት እንዲያገኙ ተደርጓል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባለፉት አምስት ዓመታት ያመጣቸውን ውጤቶች በማጠናከርና ያሉበትን ችግሮች ቀርፎ የሕዝብ አመኔታ የተቸረው አለኝታ የሆነ ተቋም እንዲሆን በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ ተገለጸ።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በለውጥ ሥራዎች አተገባበር ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትናንትናው እለት ተወያይቷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ፉዓድ ኪያር እንደገለጹት፤ ባለፉት አምስት ዓመታት የፍርድ ቤቱን ነፃነትና ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ እንዲሁም ፍርድ ቤቱን ለተገልጋዮችም ሆነ ለሠራተኛው ምቹ እንዲሆን ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል።



አቶ ፉዓድ ኪያር



አቶ ተስፋዬ ንዋይ

ባለፉት አምስት ዓመታት ከተሠሩ ሥራዎች ዋነኛው የዳኞችን ነፃነት በማስጠበቅ ዳኞችን ከማናቸውም ውጫዊና ውስጣዊ ጫና ማላቀቅ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም ዳኞች ለሕግና ለህሊናቸው ብቻ ተገዥ በመሆን ማስረጃን እና ፍሬ ነገርን መነሻ በማድረግ የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ በማስቻል ረገድ አዎንታዊ ለውጥ መምጣቱን ተናግረዋል።

የጉዳዮች መጓተትና የፍትህ መዘግየትን ለማስቀረት በተሠራ ሥራ የመዛግብት ቁጥር በእጅጉ መቀነስ መቻሉን ገልጸው ፤የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ የፍርድ ቤት መር አስማሚ ሥርዓትን በመተግበር ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሁለት ሺህ 516 መዛግብት በስምምነት እንዲቋጭ ተደርጓል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ካሉት 13 ምድብ ችሎቶች ውስጥ ሰባቱን ባለፉት አምስት ዓመታት በአዲስ መልክ የተደራጀ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ እድሳት በማድረግ የግልጽ ችሎትና የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲኖራቸው ተደርጎ ምቹና ተደራሽ አገልግሎት እየተሰጠባቸው ይገኛል ብለዋል።

ፍርድ ቤቱ ባለፉት አምስት ዓመታት ሰፊ ሥራዎችን ቢያከናውንም አሁንም ያልተሻገራቸው ችግሮች አሉ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ከዳኝነት የሙያ ብቃት እና ሥነ ምግባር ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በርካታ መሆናቸው በቀጣይ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ መሆን እንደሚኖርበት ጠቁመዋል።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም ላይ ለውጦች ያሉ ቢሆንም በቀጣይ ብዙ ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል ብለዋል። እስካሁን ያልተፈታው ሌላኛው ተግዳሮት የአስተዳደር ሠራተኞች የኑሮ እና የአቅም ማሻሻል አለመቻሉ መሆኑንም አንስተዋል።

በመሆኑም ባለፉት አምስት ዓመታት የመጡትን ውጤቶች አጠናክሮ እንዲሁም ተቋሙ ያሉበትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጀት መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።


የፍርድ ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ተስፋዬ ንዋይ በበኩላቸው ባለፉት 5 ዓመታት መዝገቦች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እልባት እንዲያገኙ ውጤታማ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸው፤ ይህም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን በአግባቡ መተግበር በመቻሉ ነው ብለዋል።

የመዝገቦች መሸጋገርም በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ለአብነትም ከ2012 ወደ 2013 ዓ.ም የተሸጋገሩ መዝገቦች 27 ሺህ ሲሆኑ ከ2015 ወደ 2016 ዓ.ም የተሻገሩ መዝገቦች ግን 14 ሺህ መሆናቸውን ገልጸዋል ።

# ተመራቂዎች በገቡት ቃልኪዳን መሠረት ያለምንም ልዩነት ሁሉንም ለማገልገል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ተመራቂዎች በገቡት ቃልኪዳን መሠረት ሁሉንም የሰው ልጆች ሁሉ በእኩልነት ለማገልገል መዘጋጀት እንዳለባቸው የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊና የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቦርድ ሰብሳቢ ዘላለም ሙላቱ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡ ኮሌጁ በተለያዩ የጤና መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ መስኮች ያሰለጠናቸውን 300 ተማሪዎች ትናንት አስመርቋል፡፡



ዘላለም ሙላቱ(ዶ/ር) በመርሀ ግብሩ ላይ ባስተላለፉት መልእክት እንዳሉት፤ የጤና ዘርፍ በርካታ የሰው ኃይል የሚፈልግ ውስብስብና ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበት የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም ተመራቂዎች በገቡት ቃልኪዳን መሠረት ሁሉንም የሰው ልጆች ሁሉ በእኩልነት ለማገልገል መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የጤና አገልግሎት በመረዳዳት፣ በትብብርና በመግባባት የሚከወን የሕይወት አድን ሥራ ነው ያሉት ዶክተር ሙላቱ፤ በሙያችሁና በጊዜያችሁ የማህበረሰቡን ያልተሟላ የጤና ፍላጎትን ለማርካት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባችኋል፡፡ አገልግሎት ስትሰጡም ቁርጠኛ፣ ርህራሄና ፍቅርን መላበስ ይጠበቅባችኋል ነው ያሉት፡፡

ሕክምና የሰው ልጆችን ሕመም መታመምንና እያንዳንዱ ነፍስ ያለውን ዋጋና ክብር አስቦ መሥራት የሚጠይቅ የሙያ ዘርፍ ነው ያሉት ቦርድ ሰብሳቢው፤ ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ውጤት መጠቀምና ራሳችሁን ለማሳደግ በመትጋት የተጣለባችሁን ሀገራዊና ሙያዊ ኃላፊነት እንድትወጡ የአደራ መልእክቴን አስተላልፋለሁ ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ ሀንጋቱ መሐመድ በበኩላቸው፤ ቢሮው በከተማዋ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና የማህበረሰቡን የጤና ፍላጎት ለማሟላት እየሠራ ነው፡፡

ለዚህም የኮሌጁ ብቁ ሙያተኞችን የማፍራት ዓላማ እንዲሳካ ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል እያደረገ ነው፡፡

ተመራቂዎችም በዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍና አስቻይ እድሎችን በመጠቀም መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱ ያላቸውን እምነት ገልጸው፤ የከተማዋን ብሎም የሀገሪቱን የጤና ሥርዓት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ እንዲተጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አለሙ ዳንኤል እንዳሉት ደግሞ፤ ኮሌጁ ከተመሠረተበት 1941 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ሙያተኞችን አፍርቷል፡፡ አሁንም እያፈራ ይገኛል፡፡

በከተማ አስተዳደሩና በሀገር አቀፍ ደረጃ በጤናው ዘርፍ ያውን የሰለጠነ የሰው ሀብት ፍላጎት ለማሟላት እየተጋ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት በመስጠት ለሀገሪቱ ብልጽግና ጉዞ ከዳር መድረስ እየተጋ ይገኛል፡፡

የእለቱ ተመራቂዎችም በቆይታቸው ያገኙትን እውቀት ተጠቅመው ማህበረሰባቸውን በቅንነትና በታማኝነት ለማገልገል ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በትናንትናው ዕለት የተመረቁ ተማሪዎች በ13 የቅድመ ምረቃና በሁለት የድህረ ምረቃ መርሀ ግብሮች ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን፤ ከተመራቂዎች ውስጥ 204ቱ ሴቶች መሆናቸው ተመላክቷል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአረንጓዴ ዐሻራው መርሀ ግብር የስኬት ጉዞ ሌላው ማሳያ

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከ32 ቢሊየን በላይ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸው ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በችግኝ ተከላው መንግሥትና ሕዝቡ ከፍተኛ የተቀናጀ ጥረት ያደረጉ ሲሆን፣ እንደ ችግኝ ተከላው ሁሉ በእንክብካቤውም ተመሳሳይ ርብርብ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም የሥነ ሕይወታዊ አፈርና ውሃ ጥበቃና የጥምር ደን እርሻ ዴስክ መረጃን ዋቢ ያደረገ ዘገባ እንዳመለከተው፤ ኅብረተሰቡ እንደ ተከላው ሁሉ ለችግኞቹ በኃላፊነት ስሜት እንክብካቤ እያደረገ ነው፤ ሚኒስቴሩ በአምስተኛው ዙር በተተከሉ የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኞች ላይ የመጀመሪያ ዙር የጽድቀት ምዘና መደረጉንም ጠቅሶ፤ በዚህም የችግኞቹ የጽድቀት ምጣኔ 90 ነጥብ አራት በመቶ መድረሱን አመልክቷል፡፡

ሚኒስቴሩ እንዳለው፤ የችግኞች የጽድቀት ምዝና በዓመት ሁለቴ የሚካሄድ ሲሆን፣ አሁን የተመዘገበው የ90 ነጥብ አራት በመቶ መጠን ከእዚህ በፊቱ የተሻለ ውጤት የታየበት ነው፡፡ የጽድቀት መጠኑ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ መጥቷል፤ ቀደም ሲል የጽድቀት መጠኑ 80 በመቶ ነበር፡፡ የዘንድሮ ከፍ ማለቱ ሥራው በእኔነት ስሜት መሠራቱን እንደሚያመለክትም ነው ሚኒስቴሩ ያብራራው፡፡

በመርሀ ግብሩ የተተከሉ የአቮካዶና አንዳንድ የፍራፍሬ ችግኞች ማፍራት ጀምረዋል፤ ምርት መስጠት መጀመር ብቻም ሳይሆን ምርታቸው ለሀገር ውስጥ እንዲሁም ለውጭ ገበያ እየቀረበም ነው፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ ችግኞች በአየር ንብረት ላይም እንዲሁ አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳደር መጀመራቸውን የደን ዘርፍ ባለሙያዎች እያረጋገጡ ይገኛሉ፡፡

የችግኞች የጽድቀት መጠን እየጨመረ መምጣትና ከችግኞቹ መካከል አንዳንዶቹ የታለመላቸውን ግብ ማሳካት መጀመራቸው ኅብረተሰቡ ለችግኞቹ የሚያደርገው እንክብካቤ በጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑን ይጠቁማል። መንግሥት ኅብረተሰቡ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩን በባለቤትነት ስሜት እንዲመራው ያከናወነው ተግባር ውጤታማ መሆኑንም ያመለክታል፡፡

በችግኞች ጽድቀት መጠን ላይ የታየው ከፍተኛ ለውጥ ትርጉሙ ብዙና በመርሀ ግብሩ ላይ እምርታ እንዲመዘገብ ማድረግ የሚያስችል ነው፤ የጽድቀት መጠኑ በእዚህ መልኩ እየተሻሻለ የሚመጣ ከሆነ፣ በመርሃ ግብሩ የተያዙትን አላማዎች አስቀድሞ በሚገባ ማሳካት ይቻላል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ የተመናመነውን የሀገሪቱን የደን ሀብት በቅርብ ጊዜ መተካት እንደሚቻል ያመላክታል፡፡

ተገቢ ችግኞች በተገቢው ሥፍራ በተገቢው ወቅት መተከላቸው፣ ከእንስሳትና ሰው ንክኪ መጠበቃቸው፣ የዝናቡ ሁኔታ ጥሩ መሆንና የመሳሰሉት ለጽድቀት መጠኑ መጨመር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደቻሉ ይገመታል።

አሁን ለታየው የችግኞች የመጽደቅ መጠን መጨመር የኅብረተሰቡ እንክብካቤ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶታል። ኅብረተሰቡ በችግኝ ተከላው ያሳየው ርብርብ በእንክብካቤውም ተጠናክሮ መቀጠሉንም ያመለክታል፡፡

ችግኞችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ በመጠበቅ ብቻ በጽድቀት መጠን ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለው ደግሞ ኅብረተሰቡ ነው፡፡ ኅብረተሰቡ ይህንን በማድረጉም ነው በጽድቀት መጠኑ ላይ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡

ከዚህ ውጭ በበጋው ወቅት የሚጥል ዝናብ ለጽድቀት መጠኑ መጨመር ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል፤ የተተከሉት ችግኞች ለመተከል የደረሱ መሆን አለመሆናቸው፣ የተተከሉበት ቦታም ለችግኞቹ ምቹ መሆን አለመሆኑም በጽድቀት መጠን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ ለጽድቀት መጠኑ ከፍተኛ መሆን የኅብረተሰቡ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ቢገለጽም፣ የተጠቀሱት ጉዳዮችም የበኩላቸውን ሚና አበርክተዋል ብሎ መውሰድ ይቻላል።

ለችግኞች የጽድቀት መጠን መጨመር ኅብረተሰቡ አሁንም ሚናውን መወጣቱን መቀጠል የሚኖርበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ ችግኞች በሚተከሉባቸው ሥፍራዎች መረጣ፣ በአግባቡ በመተከላቸውና ለተከላ ብቁ በመሆናቸው ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው ዙር የጽድቀት መጠን ምዘና ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ ግምገማ ከእስከ አሁኑም በላይ የተሻለ የጽድቀት መጠን እንዲመዘገብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ በጀት ዓመት ባለፉት ወራትና አሁንም ሲጥል የነበረውና እየጣለ ያለው ዝናብ ለችግኞች የጽድቀት መጠን መጨመር ሁነኛ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፤ በዚህ ላይ እየጎለበተ የመጣውና ከፍተኛ የጽድቀት መጠን እንዲመዘገብ ያስቻለው የኅብረተሰቡ የችግኞች እንክብካቤው ልምድ የጽድቀት መጠኑን ሊያሳድገው ይችላል።

ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው በችግኞች የጽድቀት መጠን ላይ ይህን ከፍተኛ እምርታ በማምጣት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ የተያዙ ግቦችን ማሳካት እንደሚቻል ነው፡፡ አስቀድሞ የተተከሉትን በዚህ መልኩ በመንከባከብ ለውጤት ማብቃት ከተቻለ፣ በቀጣይ የሚተከሉትንም እንዲሁ በጥንቃቄ በመትከልና በመንከባከብ በአረንጓዴ ዐሻራው ይበልጥ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

ለእዚህ ሁሉ ደግሞ የጽድቀት መጠን እንዲጨምር ከዚህ አልፎም አንዳንድ የፍራፍሬ ተክሎች ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ ያስቻሉ ሥራዎች ተሞክሮ ተቀምሮ ለቀጣይ የመርሃ ግብሩ ሥራዎች ውጤታማነት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የችግኞች የጽድቀት መጠን መጨመሩ የአረንጓዴ ዐሻራው መርሀ ግብር የስኬት ጉዞ ሌላው ማሳያ ተደርጎ መወሰድ የሚኖርበት ሲሆን፣ በቀጣይም ይሄ ስኬት እንዲመዘገብ ኅብረተሰቡ ተሳትፎ ከእነ ግለቱ መቀጠል ይኖርበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዜጎች ለብሔራዊ ምክክሩ መሳካት በህብረት ሊቆሙ ይገባል

ቲሻ ልዑል

ኢትዮጵያ ችግሮችን በራስ የመፍታት የቆየ እሴት ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ነች። ይህ ሀገር በቀል ባህል ለዘመናት ከማህበረሰቡ ጋር የኖረ ነው። ሀገሪቱን ይሄ ብቻ አይደለም ልዩ የሚያደርጋቸው። በአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘናት የሚገኙ ሕዝቦቿ እንደባህላቸው ልዩነት የችግር አፈታታቸውም በዚያው ልክ የሚለያይ ነው፡፡ ሁሉም ግን በአንድ ነገር ይመሳሰላሉ። እርሱም ሰላም የሁሉም መሠረት፤ የአንድነታቸው ምሰሶ መሆኑን ነው።

ሰላም ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ነው። በሁሉም ዘርፍ አስፈላጊ የሆነውን ማህበራዊ እሴት እውን ለማድረግ ደግሞ የእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ኃላፊነት ከፍ ያለ ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ ዜጋም ለሰላም መስፈን የነቃ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል።

ሰላም የማህበረሰቡን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚጠቅመውን ያክል ሁሉ በሰላም በማደፍረስ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቁ በርካቶች ናቸው፡፡ ከብጥብጥና ሁከት የሚያተርፉ የሴራ ፖለቲካና አሻጥር ቀማሪዎች በርካቶች ናቸው። ለአብነት ብንመለከት የሊቢያን ሰላም በማደፍረስ የጦር መሳሪያ በመሸጥ ኢኮኖሚያቸውን የሚደጉሙ ሀገራት መኖራቸው ይነገራል፡፡ ይህ ዓይነቱ የሰላም መደፍረስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዩክሬን እና ሩሲያ፣ በኢራቅ፣ በፍልስጤም እንዲሁም በእስራኤል እና ጋዛ በሚስተዋሉ ሀገራቱ ወደለየለት የጦርነት ቀጠና ተለውጠዋል፡፡ ዜጎችም በማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜያት በነበሩ በእርስ በርስ ጦርነቶች በርካታ ዜጎቿን ለማጣት ተገዳለች። የኢኮኖሚ ውድቀትና የንብረት ውድመትም አጋጥሟታል፡፡ ከነዚህ ታሪኮቻችን መረዳት የምንችለው ግጭትን በቀላሉ ማስቀረት እየቻልን በቸልተኝነት ካለፍን ሰላማችን ደፍርሶ ነጋችንን ከማበላሸት ውጭ አንዳች ነገር መፈየድ እንደማንችል ነው። በተለይ ዛሬን የቆየውን ማህበራዊ እሴቶቻችንን ተጠቅመን በራሳችን አቅምና ብልሃት የእርስ በእርስ ግጭቶቻችንን ማቆም ካልቻልን ነገ ለቁጭት መዳረጋችን አይቀርም።

አሁን አሁን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚታየው የወንድማማቾች ግጭት የሚያሳየን የሰላም መደፍረስ መኖሩን ነው። እነዚህን አለመግባባቶች ለመፍታት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ በለውጡ ማግስት በመንግስት ገለልተኛ የሆነ ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል። የኮሚሽኑ መቋቋም እንደ ሀገር ያሉብንን ችግሮች በምክክር መፍታት እንድንችል እንደ ትልቅ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይህ ርምጃ አዲስ ሀገራዊ የፖለቲካ ባህል መፍጠር እንደሚያስችልም ይታመናል፡፡

በሀገሪቱ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተፈጠሩ ልዩነቶችና አለመግባባቶች ምክንያቶችን በጥናትና በሕዝባዊ ውይይቶች በመሰብሰብ፣ በተለዩ አጀንዳዎች ላይ ሀገራዊ ምክሮችን በማካሄድ፣ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ እና ለተግባራዊነቱም የመከታተያ ሥርዓት በመዘርጋት ለሀገራዊ መግባባት ምቹ ሁኔታ መፍጠር የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ተልዕኮ ተደርጎ ተቀምጧል፡፡

የሀገራዊ ምክክር ውጤቶችን በአግባቡ መረዳት፣ የተገኙ ውጤቶች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀትና ስልቶችን መንደፍ እንዲሁም ለተግባራው ምዕራፍ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት አተገባበሩን መከታተል በምክክር ኮሚሽኑ ትኩረት የሚሰጣቸው አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ ትልቅ የሽግግር ፍኖተ ካርታ አካል ሆኖ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በፍትህ ማሻሻያ ሂደቶች የሚታጀብ ነው፤ በራሱ ፍጻሜ ሳይሆን የተቀናጀና አሳታፊ የለውጥ ሂደት ጅምር ነው፡፡

ኮሚሽኑ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለተፈጠሩ ልዩነቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በመለየት እና ውይይቶች የሚካሄዱባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በመለየት ምክክር እንዲደረግባቸው ያመቻቻል፡፡ የሚካሄዱት ሀገራዊ ምክክሮች፤ አካታች፣ ብቃት ባለውና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመሩ፣ የአለመግባባት መንስዔዎችን በትክክል በሚዳስስ አጀንዳ ላይ የሚያተኩሩ፣ ግልፅ በሆነ የአሠራር ሥርዓት የሚመሩ እና የምክክሮቹን ውጤቶች ለማስፈፀም የሚያስችል ዕቅድ ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ ሀገራዊ የምክክር ሂደት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እንዲሁም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ሥርዓት ይዘረጋል። ከምክክሮቹ የተገኙ የመፍትሔ ምክረ ሃሳቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ በዜጎች መካከል እንዲሁም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመን የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲገነባ ለማስቻል ይሠራል፡፡

ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል ለማዳበር እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምቹ መደላድል መፍጠር፤ ወቅታዊ ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ተፈተው አስተማማኝ ሰላም የሚረጋገጥበትን የፖለቲካ እና የማኅበራዊ መደላድል ማመቻቸት፤ ለሀገራዊ መግባባት እና ጠንካራ ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት ጽኑ መሠረት መጣል የምክክር ኮሚሽኑ ተጨማሪ አላማ ነው፡፡

የምክክር ኮሚሽኑ ይህንን አላማ ብቻውን ከግብ ለማድረስ አይችልም፡፡ ለስኬታማነቱ መንግስት፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ምሁራንና መላው ሕዝብ በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል። በያገባኛል መንፈስ፤ የሰላማችን ባለቤቶች ለመሆን በቁርጠኝነት መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ከልዩነቶች ሁሉ በላይ ገዝፎ በሁሉም ልብ ተመሳሳይ ስፍራ ይዞ ለሚገኘው የጋራ ሰላማችን በአንድነት ልንቆም ይገባል፡፡ የተለየ የፖለቲካ አቋምም ሆነ የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው ዜጎች ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተው አንድነት በሚፈልጉ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በአንድነት ሲሰሩ አይተናል። ይህንን አቅማችንን ሰላማችንን ለማረጋገጥና ችግሮቻችንን በውይይት ለመፍታት ልንጠቀምበት ይገባል።

ለዚህ ሁነኛ ምሳሌ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የሕዳሴ ግድብ ነው፡፡ ከዓመታት በፊት የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ወደ ትግበራ ሲገባና ሀገሪቱ ግድቡን የምትገነባው በራሷ አቅም እና ወጪ መሆኑ ሲታወቅ፤ ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ለግድቡ ግንባታ በአንድነት ቆሟል፡፡ ግንባታውም እስካሁንም እየተከናወነ ይገኛል።

እስካሁን በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩነቶች ቢኖሩንም ለግድቡ ድጋፍ ማድረጋችንን አላቆምንም። ምክንያቱም የግድቡ ጉዳይ ከልዩነታችን በላይ ከመሆኑም በተጨማሪ ለትውልድ የምናስተላልፈው ትልቅ ቅርስና ታሪክ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ አንድነትም ፍሬ አፍርቶ ውጤቱን ለማየት ወደ መጨረሻው ምዕራፍ እየደረስን እንገኛለን፡፡

በመሆኑም ለሕዳሴው ግድብ በአንድነት እንደቆምን ሁሉ ለሰላም መስፈን አስፈላጊ ለሆነው ምክክርም በአንድነት መቆም ይኖርብናል፡፡ ልዩነቶችን በመነጋገር ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሁሉም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽኑም ባስቀመጠው አላማ መሠረት የሚካሄዱት ሀገራዊ ምክክሮች፤ አካታች፣ ብቃት ባለውና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመሩ፣ የአለመግባባት መንስዔዎችን በትክክል በሚዳስስ አጀንዳ ላይ የሚያተኩሩ፣ ግልፅ በሆነ የአሠራር ሥርዓት የሚመሩ እና የምክክሮቹን ውጤቶች ለማስፈፀም የሚያስችል ዕቅድ ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ውጤታማ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ዜና

# በኦቲዝም ጥላ ስር የሚኖሩ ልጆች ለውጤት እንዲበቁ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተገለጸ

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በኦቲዝም ጥላ ስር የሚኖሩ ልጆች ያላቸውን ክህሎት በመለየት ለውጤት እንዲበቁ ሁለተናዊ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተጠቆመ።ሻምፒዮንስ አካዳሚ 17ኛውን የኦቲዝም የግንዛቤ ማስጨበጫ ቀን ትናንት ተማሪዎችና ወላጆች በተገኙበት በተለያዩ መርሀ ግብሮች አክብሯል።

በወቅቱ የሻምፒዮንስ አካዳሚ ባለቤትና የአዕምሮ ሕክምና ባለሙያዋ ዶክተር መአዛ መንክር እንደገለጹት፤ በኦቲዝም ጥላ ስር የሚኖሩ ልጆች አስፈላጊውን ድጋፍ ካገኙ ለውጤት መብቃት ይችላሉ፤ በኦቲዝም ጥላ ስር የሚኖሩ ልጆች የንግግር ክህሎትን ማሳደግ፣ የባህሪ ማረቅ፣ የማህበራዊ ክህሎት ማደግ ከወላጆቻቸውና ከአካባቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ድጋፎችን ይፈልጋሉ፡፡

ኦቲዝም እንዳለባቸው የተረጋገጠባቸውን ልጆች አካዳሚው ክህሎታቸውን በመለየትና ለወላጆቻቸው



ዶክተር መአዛ መንክር

ስልጠና በመስጠት የማብቃት ሥራ እየሠራ መሆኑን ዶክተር መአዛ ጠቁመው፤በኦቲዝም ጥላ ስር የሚኖሩ ልጆች ያላቸውን ክህሎት በመለየት ለውጤት እንዲበቁ ድጋፍ የተለያዩ ድጋፎች ሊደረግላቸው እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

ድጋፉ በአንድ ጊዜ የሚሆን ሳይሆን ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ለወላጆች በማስረዳት በትግስት ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው እየተደረገ ገልጸው፤ አካዳሚው በኦቲዝም ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ከማስጨበጥ በዘለለ በኦቲዝም ጥላ ስር ያሉ ሕፃናትን ከመደበኛ ተማሪዎች ጋር አካቶ በማስተማር አመርቂ ውጤት በማምጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በኦቲዝም ጥላ ስር የምትኖር የሰባት ዓመት ሴት ልጃቸው ትምህርቷን በሻምፒዮንስ አካዳሚ እየተከታተለች መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ ራሄል፤ ልጃቸው ወደ አካዳሚው ከመምጣቱዋ በፊት መናገርም ሆነ ሌሎች ተግባራትን እንደማታከናውን ጠቁመዋል፡፡

አሁን ላይ በርካታ ለውጦችን በማምጣት በዚሁ ዓመት የቅድመ መደበኛ ትምህርቱዋን በማጠናቀቅ እንደምትመረቅ ተናግረው፤ ልጆቻቸው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ተቋማት በመውሰድ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ እንደሚገባ መክረዋል፡፡

ወይዘሮ እምነት ጫንያለው በበኩላቸው፤ ከዚህ ቀደም ልጃቸው ምግብ አለመብላት፣ መጮህና የመሳሰሉ ተግባራትን እያከናወነ የነበረ በመሆኑ አውስተው፤ አካዳሚው በሠራው ሥራ ልጃቸው በመረጋጋቱ እሳቸውም እረፍት እንዳገኙ ተናግረዋል፡፡

ልጃቸው ራፋኤል ዮናስ እንደሌሎች ልጆች በአግባቡ የመጫወት፣ የመመገብና ሌሎች የእለት ተዕለት ተግባሩን እያከናወነ መሆኑ ተስፋ እንደሰጣቸው አንስተው፤ ከባድ ቢሆንም ወላጆች ጉዳዩን አምኖ በመቀበል የልጆቻቸው ሁኔታ ሳይባባስ ወደ መፍትሔ ልሄዱ እንደሚገባ ወይዘሮ እምነት አመልክተዋል፡፡

አካዳሚው ካለፉት 16 ዓመታት ጊዜ ጀምሮ በኦቲዝም ጥላ ስር ለሚኖሩ ሕፃናትና ወላጆቻቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን ሲሰጥ መቆየቱ ታውቋል፡፡

## የአትክልትና የፍራፍሬ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአትክልትና የፍራፍሬ ምርቶች ማለትም ቲማቲም ፣ ሽንኩርት፣ ጥቅል ጎመን፣ የተለያዩ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ደርሰው ለገበያ እየቀረቡ በመሆናቸው በአሁኑ ጊዜ የዋጋ ንረቱ ተረጋግቷል ብለዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በጥናት፣ በምርምርና በተመረጡ አካባቢዎች ላይ በስፋት የማምረት ሥራ በመሥራት ምርታቸውን በእጥፍ የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ከበደ፤ የተትረፈረፈ ምርት ለገበያ በመቅረቡም የአትክልትና የፍራፍሬ የዋጋ ንረት ተረጋግቷል ብለዋል፡፡

የአትክልትና የፍራፍሬ ገበያ ዋጋ መረጋጋት ምክንያትም ባሉት ሦስት የምርት ወቅቶች ማለትም የበጋ መስኖ ልማት፣ የበልግና የመኸር ወራቶች ላይ ያሉ የውሃ አማራጮች ፣የእርሻ መሬቶችና ያለውን የሰው ኃይል በመጠቀም በስፋት የማምረት ሥራ በመሠራቱ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአትክልት፣የፍራፍሬ፣ የአገዳ፣ የብርዕና የጥራጥሬ ምርትና ምርታማነትን በእጥፍ ለማሳደግ በስፋት እየተሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የበጋ መስኖ ልማት በአትክልት፣ በፍራፍሬና በስንዴ ምርት ላይ ከፍተኛ ውጤት እያስገኘ ነው ብለዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ የዋጋ ንረት መረጋጋት ከበጋ የመስኖ ስንዴ ጎን ለጎን ውሃማ አካባቢዎችን በስፋት የማምረት ሥራ በመሠራቱም ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አሁን እየታየ ያለውን የአትክልትና የፍራፍሬ ምርት የዋጋ መረጋጋት ባለበት ለማስቀጠል መጠነ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ እየተሠሩ ካሉት ሥራዎች መካከል የውሃ አማራጮችን፣ ያለውን የሰው ኃይልና የመሬት ሀብት በትክክል በመጠቀም ምርትና ምርትማነትን ለማሳደግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡

አትክልትና ፍራፍሬን በበጋ መስኖ፣ በበልግና በክረምት ዝናብ አርሶ አደሮች በስፋት እንዲያመርቱና ተጠቃሚነታቸውን እንዲያሳድጉ የማሳደግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝም ጠቅሰዋል፡፡ ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡

## የሥርዓተ ምግብና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዋስትናን ማረጋገጥ ተገቢ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ እነዚህ ይፋ የተደረጉት ስትራቴጂዎች የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ሽግግርን ለማሳለጥ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል።

ይህንን በመገንዘብ ባለድርሻ አካላት ለስትራቴጂዎቹ ተፈጻሚነት የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትና መጓደል ችግር የሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ “ከማምረት በላይ” በሚል መሪ ቃል የምግብ እና የሥርዓተ-ምግብ መርሀ-ግብር ቀርጾ ተግባራዊ እያደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

መንግሥት ምርትና ምርታማነት ለመጨመር እና በምግብ ራስን ለመቻል ባደረገው ጥረት አመርቂ ለውጦች ሊመዘገቡ ችለዋልም ብለዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የምግብና ሥርዓተ ምግብ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ አለምፀሐይ ስርጋዊ በበኩላቸው፤ስትራቴጂዎቹ በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱ ምርቶች ማህበረሰቡ ጋር ሲደርሱ ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሆን እንዲሁም ምርቶች እንዳይባክኑ ያደርጋል ብለዋል።

ይህም በግብርናው ዘርፍ በምግብ ንጥረ ነገር የበለፀገ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፤ የተሰባጠረና በቂ ምግብ አቅርቦት፤ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት እንዲኖር ያስችላል ያሉት ኃላፊዋ፤ ስለጉዳዩ አሳሳቢነትና የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ከዚህም ባለፈ ሥርዓተ ምግብ ተኮር የግብርና ልማት ሥራዎችን ለመተግበር እና አመቺ ሁኔታዎች በመፍጠር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል። ይህም የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል።

## ኃይል ማመንጫ ጣቢያው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጣቢያው የውስጥ አቅሙን ተጠቅሞ ባከናወናቸው የጥገና ሥራዎች ሙሉ ለሙሉ ቆሞ የነበረ አንድ ተርባይን እና የማምረት አቅማቸው ዝቅ ብሎ የነበሩ ሁለት ተርባይኖችን በመጠገን ኃይል ወደ ማምረት አቅማቸው እንዲመለሱ አድርጓል።ይህም ተቋሙ በውጭ ሀገር ሙያተኞች ቢያሰራቸው ኖሮ ከ75 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ሊጠይቅ ይችል ነበር።

የውሃ መጠንን ለመቀነስና ለመጨመር የሚያገለግሉት የተርባይኑ አካሎች (nozel) በውሃ ግፊት፣ በጠጠርና በአፈር የተበሉ በመሆናቸው ጣቢያው ኃይል የማመንጨት አቅሙ ቀንሶ እንደነበር ኃላፊው ጠቅሰዋል።

ግልገል ጊቤ -2 ካሉት አራት ተርባይኖች ሦስቱ ተጠግነው በሙሉ አቅማቸው መሥራት በመቻላቸው አሁን የጣቢያው የማመንጨት አቅሙ ወደነበረበት መመለሱን ገልጸው፤ ተርባይኖቹ ተጠግነው ወደ መጀመሪያው ቁመናቸው በመመለሳቸው፤ ኃይል ሳያመነጭ ያልፍና ይባክን የነበረው ውሃ ኃይል እያመነጨ እንዲያልፍ ሆኗል ብለዋል።

የጥገና ሥራው ለውጭ ሀገር ዜጎች ይሰጥ ቢባል የመጠገን ሳይሆን የመለወጥ ሥራ ስለሚሠራ ለመለዋወጫ እቃ ግዢና ለሙያተኞች ከፍተኛ ወጪ ይወጣ እንደነበር ኢንጂነር ሹመት ገልጸዋል።

የጣቢያው ሠራተኞች የመጠገን ተነሳሽነትና ፍላጎት አሳይተው ሥራውን በኃላፊነት በመረከብ ሦስት ተርባይኖችን ጠግነው ወደ ሥራ በማስገባት በራስ የመተማመን አቅም ማረጋገጫ መሆኑን አስረድተዋል።

በቀጣይም ከ105 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ወደ 80 ሜጋ ዋት የወረደውን አራተኛውን ተርባይን ለመጠገን ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ኢንጂነር ሹመት ጠቁመው፤ አራተኛው ተርባይን ተጠግኖ ወደ ሥራ ሲገባ ጣቢያው በድምሩ ለተርባይኖች ጥገና ያወጣ የነበረውን መቶ ሚሊዮን ብር የሚያስቀር ይሆናልም ብለዋል።

እንደ ተቋም የጥገና ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚከናወን የተናገሩት ኢንጂነር ሹመት፤ ጣቢያው በሌሎች ጣቢያዎች ከሚገኙ ሙያተኞች ጋር ልምድ የመለዋወጥና የመተጋገዝ ሥራ እንደሚሠራ አስረድተዋል።

የግልገል ጊቤ-1 ጣቢያ ሠራተኞች ወደ ግልገል ጊቤ 2 ፤ የግልገል ጊቤ 2 ሠራተኞችም ወደ ተለያዩ ጣቢያዎች በመሄድ በጥገና ሥራዎች ላይ እንደሚሳተፉ ጠቁመው፤ ይህንን የመተጋገዝ ባህል በማሳደግ ብልሽቶችን በራስ አቅም የማከናወኑ ተግባር የሚቀጥል እንደሆነም ጠቅሰዋል።

በጣቢያው የተከናወኑ የማዘመን ሥራዎች በተርባይኖች ላይ ለሚያጋጥሙ ብልሽቶች ጥቆማ የሚሰጡና የጥገና ሥራውን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ጣቢያው የተላበሰ መሆኑን አስረድተዋል።

ጀማሪ መሐንዲሶችም በልምድ ልውውጥና በሥልጠና ራሳቸውን እንዲያበቁ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ወጣት መሐንዲሶች ለቴክኖሎጂ ቅርብ እንደመሆናቸው እድሉ ቢሰጣቸውና በነጻነትና በኃላፊነት እንዲሠሩ ቢደረግ የጥገና አቅምን የበለጠ ማሳደግ ይቻላል ብለዋል።

የግልገል ግቤ-2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ሥራ የጀመረው በ2002 ዓ.ም ሲሆን፤ እያንዳንዳቸው 105 ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጩ አራት ተርባይኖች ያሉትና በድምሩ 420 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው ነው።

## “በኢ-መደበኛ ንግድ የተደራጀን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብሏል።

አራት ኪሎ ግንፍሌ አካባቢ በኢ-መደበኛ ንግድ በአልባሳት ንግድ ተደራጅቻለሁ የሚሉት አቶ ስመኘው ጥላሁን ለኢፐድ እንደገለጹት፤ በ2005 ዓ.ም ከተማ አስተዳደሩ የጎዳና ንግድ ሥርዓት መያዝ አለበት በሚል ባወጣው አሰራር መሠረት በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ መደራጀታቸውን ነው የገለጹት።

በዚህም ኢ-መደበኛ ግብር ከፋይ ተብለው በሕጋዊ ሥርዓት የንግድ ሥራ ላይ እንደተሰማሩ የገለጹት አቶ ስመኘው፤ ይህ አሠራር ከጎዳና ንግድ መከራና ስቃይ እንደታደጋቸው ተናግረዋል። በዚህም ሥራ ለአሥራ አንድ ዓመት ቤተሰባቸውን ማስተዳደር እንደቻሉ ገልጸዋል።

“አሁን ላይ የልማት ተነሺ ስንሆን የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ነዋሪ ባለመሆናችን ምትክ ቦታ ሊሰጠን አልቻለም” ያሉት አቶ ስመኘው፤ “ለዓመታት ወረዳውና ክፍለ ከተማው አደራጅቶን ስንሰራ መቆየታችን የማይካድ ሀቅ በመሆኑ ለጉዳዩ የሚመለከተው አካል መፍትሔ እንዲሰጠን እንሻለን” ብለዋል።

ሌላኛው በኢ - መደበኛ ንግድ ላይ የተሰማሩት አቶ ካብቱ ሽኩር በበኩላቸው፤ በኢ-መደበኛ ንግድ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ መደራጀታቸውን ገልጸዋል። ከዚያም ወረዳው ከኢ-መደበኛ ንግድ ወደ መደበኛ ንግድ ሊያሳድገን ሁሉንም መስፈርቶች እንድናሟላ አሳስቦናል ብለዋል።

በዚህ መሠረት ከወረዳው መታወቂያ ውጪ ሁሉንም መስፈርቶች እንዲሁም የሲኦሲ ፈተናን ጨምሮ አስፈላጊውን መረጃዎች ለወረዳው አስገብተናል ያሉት አቶ ካብቱ፤ ወረዳው እኛን ጨምሮ ለ49 ሰዎች ኮንቴነር ለመስጠት ስም ዝርዝር አውጥቶ ነበር። በዚህም ቅሬታ ያለባቸው ሰዎች ጉዳዩን እንዲመረምሩ እድል መስጠቱን ገልጸዋል።

ይህ ሁሉ ነገር ሲሆን ወረዳው፣ ክፍለ ከተማው፣ የብሎክና የቀጣና ተወካዮች እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚያውቁም ተናግረዋል።

በከተማዋ እየተከናወነ ያለው የልማት ሥራዎች ይበል የሚያሰኙና ድንቅ እንዲሁም ለቀጣይ ትውልድ ጠቃሚ የሆኑ ናቸው። ነገር ግን በኢ-መደበኛ ንግድ የተሰማራን ግብር ከፋዮች ያሉብንን ችግሮች የሚመለከተው አካል እንዲያይልን እና መፍትሔ እንዲሰጠን እንጠይቃለን ያሉት ደግሞ አቶ ነስሩ አህመድ እና አቶ አሸናፊ ጸጋዬ ናቸው።

ከተማ አስተዳደሩ በበኩሉ በክፍለ ከተማው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ለከንቲባ ጽህፈት ቤት አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ ብሏል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ ቅሬታ አቅራቢዎችን በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡበት መልስ እንደገለጹት፤ የልማት ተነሺዎች የሚያነሷቸውን ቅሬታ አድምጠን ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነን። ለዚህም ሲባል ከከተማ አስተዳደሩ እስከ ክፍለ ከተሞች ድረስ የቅሬታ አቤቱታ አደረጃጀት ተቋቁሟል ብለዋል።

ምናልባት በክፍለ ከተማው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ለከንቲባ ጽህፈት ቤት አቤቱታቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ የገለጹት አቶ ሞገስ፤ በከተማዋ ልማት ከመኖሪያ አካባቢያቸው፣ ከንግድ ሥራቸውና ከሥራ ቦታቸው የተነሱ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማህበራት አሉ። በዚህ ሂደት ለሁሉም ተገቢ የሆነ ምላሽ መሰጠቱን ተናግረዋል።

የከተማዋ ልማት የሚነካቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎችን በአግባቡና በሥርዓቱ መሠረት መልስ እንዲያገኙ አመራሩ በቁርጠኝነት ሠርቷል፤ እየሠራም ይገኛል ብለዋል።


አቶ ሞገስ አያይዘውም፤ በከተማ ደረጃ 249 የሚደርሱ የልማት ተነሺዎች ቅሬታዎች አቅርበዋል። ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ቅሬታዎች ምትክ ቤት ከተሰጣቸው ሰዎች ጋር የተያያዘ ነው። በተለይ በእጣ 6ኛ እና 5ተኛ ፎቅ ላይ ቤት የደረሳቸው የልማት ተነሺዎች የቤት ቅያሪ መጠየቃቸውን ገልጸው፤ መፍታት የሚቻለውን ቅሬታ በተገቢው መልኩ እየተፈታ መሆኑን ተናግረዋል።

ከቀረቡት 249 ቅሬታዎች ውስጥ 83 ለሚሆኑት ምላሽ ተሰጥቷል። 54 ቅሬታዎች መረጃ የማጣራት ሥራ የሚፈልጉ በመሆናቸው በሂደት ላይ ይገኛሉ ያሉት አቶ ሞገስ፤ 176 የሚደርሱ ቅሬታዎች ትክክለኛ ያልሆኑና አግባብነት የሌላቸው እንደሆኑ ለቅሬታ አቅራቢዎች በማስረዳት የተፈቱ መሆናቸውን ገልጸዋል። በዚህም ኅብረተሰቡ ደስተኛ መሆኑን ተመልክተናል ብለዋል።

በአጠቃላይ የቀረቡት ቅሬታዎች ልማቱ በልዩ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎለት የተጀመረ መሆኑን ያሳያሉ ሲሉ ተናግረዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

## ነገረ ቲክቶክ

**የምዕራባውያንን አመኔታ ለማግኘት ከፍተኛ ወጭ አውጥቶ የተጠቃሚዎችን መረጃ አሜሪካ በሚገኝ ሰርቨሩ ለብቻ ማስቀመጡንና ከቻይና ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ጉዳውን ከፍቶ ከፈለጋችሁ መጥታችሁ አረጋግጡ ቢልም በጀ ያለው አልተገኘም። አሜሪካና አጋሮቿ ግን ቲክቶክን ሞኝህን ፈልግ። አትድከም። አናምንህም። ይልቅስ በአሜሪካ ያለውን ድርሻህን ሽጠህ ራስህን አድን እያሉት ነው**

**(የመጀመሪያ ክፍል)**

የቲክቶክ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሹ ዚ ቺው፤ ቲክቶክን የሚያግደው ረቂቅ ሕግ ለሌሎች የማኅበራዊ ሚዲያዎች ጉልበት የሚሰጥ ከመሆኑ ባሻገር፤ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ አሜሪካውያንን ከሥራ ውጪ ያደርጋል ሲሉ ያስጠንቅቃሉ። በነገራችን ላይ የቻይና መንግስት የማንንም የግል መረጃ ጠይቆን የማያውቅ ቢሆንም የአሜሪካውያን መረጃዎችን በአስተማማኙ የኦራክል ክላውድ ቋት ነው የሚከማቸው ይላሉ ቺው።

ቻይና ቲክቶክን ተጠቅማ ጸረ አሜሪካዊ የሆነ ፕሮፓጋንዳ ልትነዛ ትችላለች ስለሚባለውም ዋና ስራ አስፈጻሚው ሲመልሱ፣ 60 በመቶ የሚሆኑት የቲክቶክ ባለቤቶች እኮ ቻይናዊ አይደሉም። መረጃን ሆነ ብሎ ማዛባትም ሆነ ፕሮፓጋንድ ቲክቶክ ላይ ቦታ የለውም ሲሉ ቺው ይገልጻሉ። አሜሪካ በተደጋጋሚ ቲክቶክን ለመግዛት ስላቀረበችው ጥያቄ ዋና ስራ አስፈጻሚው ሲመልሱ ቲክቶክ አይሸጥም አይለወጥም ሲሉ እቅጩን መልሰዋል።

ሆኖም ባይትዳንስ፤ ቲክቶክን መሸጥ ከፈለገ ከቻይና መንግሥት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። ነገር ግን ቤይጂንግ ይህን እንደማታደርግ እያስጠነቀቀች ነው። አሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ የቲክቶክ ተጠቃሚዎች አዲሱን ረቂቅ አዋጅ እየተቃወሙት ይገኛሉ። ቲክቶክ 170 ሚሊዮን የሚሆኑ በአሜሪካ የሚገኙ ተጠቃሚዎቹ ወደ ግዛቶታቻቸው ተወካዮች ደውለው ረቂቁን ሕጉን ውድቅ እንዲያደርጉት እንዲጠይቁ መክሯል።

ቲክቶክ ሕንድ ውስጥ ታግዷል። ሕንድ የቲክቶክ ትልቋ ገበያ ነበረች። ነገር ግን በአውሮፓውያኑ 2020 መተግበሪያውን አግዳዋለች። እንዲሁም በኢራን፣ በኔፓል፣ በአፍጋኒስታን እና በሶማሊያ ጥቅም ላይ እንዳይውል እግድ ተጥሎበታል። በዩናይትድ ኪንግደም ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች እና የፓርላማ አባላት በሥራ ስልካቸው ቲክቶክን እንዳይጠቀሙ ባለፈው ዓመት ተነግሯቸዋል። የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽንም በተመሳሳይ በሥራ ስልክ ቲክቶክን መጠቀም አግዷል።

ቢቢሲ በደኅንነት ስጋት ምክንያት ሠራተኞቹ ከድርጅቱ የተሰጣቸውን ስልክ ተጠቅመው ቲክቶክን እንዳይገለገሉ ከልክሏል። የቲክቶክ ዋናው መሣሪያ አልጎሪዝም (ስልተ ቀመር) ነው። ይህ መተግበሪያው የተጠቃሚዎችን ታሪክ ተመልክቶ የትኛውን ዓይነት ይዘት ይወዳሉ የሚለውን የሚለይበት ዘዴ ነው። ወደ ቲክቶክ ሲገቡ ከላይ ሦስት ንዑስ ርዕሶችን ያገኛሉ። ፎሎዊንግ፣ ፍሬንድስ እና ፎር ዩ ይባላሉ። ፎሎዊንግ እና ፍሬንድስ ተጠቃሚዎች ከሚከተሏቸው ሰዎች እና ከጓደኞቻቸው የሚያገኟቸው ይዘቶች ናቸው። ፎር ዩ የተሰኘው ደግሞ ቲክቶክ በራሱ መጥኖ ተጠቃሚዎች ይህን ይዘት ይወዱታል በሚል የሚለቀቅ ነው።

ተቺዎች ቲክቶክ ከሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች በላይ የተጠቃሚዎችን መረጃ ይሰበስባል፤ ለዚህም ነው የተመረጡ ይዘቶችን የሚያቀርበው ይላሉ። የተጠቃሚዎች አድራሻ፣ የሚጠቀሙበት ስልክ፣ የሚወዷቸው ይዘቶች እና ሲፅፉ የሚያሳዩት ባሕሪን ይሰበስባል የሚል ትችት ያቀርባሉ። ገር ግን ሌሎች እንደ ፌስቡክ እና ኢንስታግራም ያሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎችም ይህን በማድረግ ይታወቃሉ። የዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲከኞች አዲስ ረቂቅ ሕግ አውጥተው ቲክቶክ መታገድ አለበት አሊያ ደግሞ ባለቤቱ የቻይናው ኩባንያ ሊሸጠው ይገባል የሚል ክርክር ገጥመዋል።

የቪዲዮ ማጋሪያ የሆነው መተግበሪያ በመላው ዓለም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተጠቃሚዎች አሉት። ነገር ግን የደንበኞቹ የመረጃ ደኅንነትን እየጠበቀ አይደለም፤ ከቻይና መንግሥት ጋር ግንኙነት አለው የሚሉ ክሶች ይቀርቡበታል። ከሁለቱም የአሜሪካ አውራ ፓርቲ የተውጣጡ ፖለቲከኞች አዲስ ያረቀቁት ሕግ የቲክቶክ ባለቤት የሆነው ባይትዳንስ መተግበሪያውን ቻይናዊ ላልሆነ ኩባንያ ካልሸጠ ይዘጋል ይላል።

ሕግ አውጪዎቹ ቲክቶክ በአሜሪካ የሚገኙ 170 ሚሊዮን ደንበኞችን መረጃ ለቻይና መንግሥት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል የሚል ስጋት አላቸው። ቲክቶክ ግን የውጭ ሀገር መረጃ ለቻይና መንግሥት አሳልፌ አልሰጥም ሲል ያስተባብላል። የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ኮንግረስ ባለፈው ሳምንት በ352 የድጋፍ ድምፅ እና በ65 ተቃውሞ ሕጉን አፅድቋል። አሁን ረቂቅ አዋጁ ወደ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ወይም ሴኔት ተላልፏል።

ነገር ግን ሴኔቱ እንደ ኮንግረሱ ሕጉን በቀላሉ ያፀድቀዋል የሚል ግምት የለም። አብዛኞቹ የሴኔት አባላት ሕጉን ይደግፉታል ወይ? የሚለው ጥያቄ ግልፅ ምላሽ አላገኘም። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ሕጉ በሴኔቱ ከፀደቀ ፊርማቸውን እንደሚያኖሩ ቃል ገብተዋል። አዋጁ በሴኔቱ ፀድቆ የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ፊርማ ካረፈበት፤ ባይትዳንስ ቲክቶክን ለመሸጥ የስድስት ወራት ዕድሜ ይሰጠዋል፤ ካልሆነ ከአሜሪካ ገበያ ይታገዳል። ቲክቶክ አሜሪካ ውስጥ ታገደ ማለት ተጠቃሚዎች መተግበሪያውን ከሚያወርዱበት የአፕ ስቶር እና የጎግል ፕሌይ ይወገዳል ማለት ነው።

ረቂቅ አዋጁ በውጭ አካላት የሚመሩ መተግበሪያዎችንም አሜሪካ ውስጥ አፕዴት ማድረግ እና መጠገን አይቻልም ይላል። ቲክቶክ በምዕራባውያን ስክሪን መቆየት የሚፈልግ ከሆነ ከእናት ሀገሩ ቻይና ጋር መቆራረጥ አለበት ይለናል የምዕራባውያን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ልሳን የሆነው "The Economist" መጽሔት በሰሞነኛ ዕትሙ። በፊት የቲክቶክ ሱስ አስያዥ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች ዕንቅልፍ የሚነሱት ተጠቃሚዎችን ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ፖለቲከኞችንና የሕዝብ እንደራሲዎችን ጭምር እንቅልፍ እየነሱ ነው።

የአሜሪካ ሴናተሮችም ሆኑ የኮንግረስ አባላት ቲክቶክ ከቻይና ጋር ባለው ግንኙነት የተነሳ ዕንቅልፍ ወይም እረፍት ካጡ ሰነባበቱ። ባለፈው መጋቢት መጀመሪያ የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዱላ ቀረሽ እሰጥ አገባ ካካሄደ በኋላ ቲክቶክ ከቻይና ባለቤቱ "ባይትዳንስ" ጋር ሰማኒያውን ቀዶ ፍች እንዲፈጽም የሚያስገድድ ሕግ አውጥቷል። አዎ ! ከቻይና ውጭ ላለ ዜጋ ወይም ኩባንያ እንዲሸጥ፤ ይህን አሻፈረኝ የሚል ከሆነ ደግሞ በአሜሪካ እንዲታደግ ኮንግረሱ ወስኗል።

"ባይትዳንስ" ለመሸጥ የማይስማማ ከሆነ የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ ወይም ሴኔት ውሳኔውን አጽድቆ ቲክቶክን ከአሜሪካውያን እስክሪን ያግደዋል። ይህን የአሜሪካ ውሳኔ ፈለግ ደግሞ የአአውሮፓ ሕብረት እንግሊዝ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ወዘተረፈ መከተላቸው ስለማይቀር በዓለማችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተወዳጅነትን ያተረፈው የቲክቶክ አዝጋሚ ግብዓተ መሬት ተጀመረ ማለት ነው።

ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ግን ቲክቶክ ላይ የተፈጠረው ስጋት ሳይጋነን አልቀረም ይላሉ። የተጠቃሚዎቹን መረጃ ለቻይና መንግስት ስለላና ጸረ አሜሪካዊ የሆነ ሀሰተኛ መረጃ ለማሰራጨት ይጠቀማል የሚለው ክስ እስካሁን ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ ማስረጃ አልቀረበበትም ይለናል መጽሔቱ። የተጠቃሚዎችን መረጃ እንደነ ፌስቡክ ለገበያ ሽያጭ ወይም ለማርኬቲንግ መጠቀሙ ለቲክቶክ ሲሆን ለምን ሀጢያት ይሆናል በማለት የሚሞግቱም አሉ።

የቻይና ሰላዮች የአሜሪካውያንን መረጃ ለማግኘት የበዛ አማራጭ እንዳላቸው፤ ከፈለጉም በቀላሉ መግዛት የሚያስችል አሰራር መኖሩም እየታወቀ ቲክቶክን እንዲህ ያለ ውዝግብ ውስጥ ማስገባት ውሳኔውን ፖለቲካዊ አንድምታ ይሰጠዋል። ቲክቶክ ተዘጋ ማለት ቻይና በምትወስደው አጸፋዊ እርምጃ አሜሪካና ምዕራባውያን ከቻይና የዲጂታል አገልግሎት ጋር ያላቸው ግንኙነት ክፉኛ ተጎዳ ማለት ነው ሲሉ የሚያስጠነቅቁ የዘርፉ ሊቃውንት አሉ። ይልቁን ቲክቶክ በማህበራዊ ሚዲያው ፉክክር እንዲኖር የተጫወተው ሚና ሌሎች ለፈጠራ እንዲነሳሱ አድርጓል።

ለምሳሌ ባለፈው ዓመት በተጠቃሚዎች በብዛት ዳውንሎድ ከተደረጉ 10 መተግበሪያዎች ስድስቱ የሜታ ወይም የፌስቡክ ባለቤት ማርክ ዙከርበርግ ናቸው። ቲክቶክ ከኋላ ተነስቶ በተጠቃሚዎች ዘንድ ተወዳጅ በመሆኑና ዳውንሎድ በመደረግ ቀዳሚ ስለሆነ ሜታንና ሌሎችን ለፈጠራ አነሳስቷል። በዚህ ደግሞ ተጠቃሚ የሚሆኑት ደንበኞች ወይም ሸማቾች ስለሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው ይለናል The Economist።

ለነገሩ ይለናል መጽሔቱ አሜሪካ ቲክቶክን እንደስጋት ብታየው አይፈረድባትም። በአሜሪካ ብቻ ተጠቃሚዎች 170 ሚሊየን ደርሰዋል። እድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች ከሆኑ ሲሶው ወይም ሶስት እጁ ቲክቶክን ለመዝናኛ ብቻ ሳይሆን እንደ መረጃ ምንጭ ይጠቀሙበታል። ይህ ነው እንግዲህ ቻይና ቲክቶክን ሀሰተኛ መረጃንና ፕሮፓጋንዳን ለማሰራጨት እንደ መሳሪያ ልትጠቀምበት ትችላለች የሚል ስጋት የፈጠረው።

ሀገራችንን ጨምሮ ብዙ ሀገራት የሚዲያ ባለቤትነት በውጭ ዜጎች እንዳይያዝ የሚከለክል ሕግ አላቸው። ታዋቂው የበርካታ ሚዲያዎች ባለቤት ሩፐርፐ መርዶክ "ፎክስ"ን ከመግዛቱ በፊት ዜግነቱን አሜሪካዊ አድርጓል። የዱባይ ንጉሳዊ ቤተሰብ ታዋቂውን የእንግሊዝ ጋዜጣ "ቴሌግራፍ"ን ለመግዛት ያደረገው ጥረት ሳይሳካ የቀረው በዚሁ የዜግነት ጉዳይ ነው። የቲክቶክ ተቀባይነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከመደበኛው ሚዲያ በላይ ተዘውታሪና ተመራጭ መሆኑ ምዕራባውያንን ክፉኛ አስግቷቸዋል።

ሀገራት መደበኛ ሚዲያው በውጭ ዜጋና ኩባንያ እንዲያዝ እንደማይፈልጉት ሁሉ በማህበራዊ ሚዲያ ባለቤትነት ላይም ተመሳሳይ አቋም ሊከተሉ ይገባል ይለናል The Economist መጽሔት። ማህበራዊ ሚዲያው ከምንም በላይ ጥንቃቄ ይፈልጋል። የአንድ ጋዜጣ ወይም ቴሌቪዥን አዘጋጆች በግላጭ ሲታወቁ በአንጻሩ ቲክቶክ ግን ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ በፍላጎቱ መሠረት የተቀመረን መረጃ ቢያደርስም እንደ መደበኛ ሚዲያው አዘጋጆች ክትትል ሊያደርጉ አይችሉም።

አንዳንድ ጥናቶች ቲክቶክ በጋዛ ላይ ሚዛናዊነት የጎደላቸውን ይዘቶችን አሰራጭቷል ሲሉ ሲከሱት ይደመጣል። ይዘቶቹ ለተጠቃሚዎች እየደረሱ ያሉት ፍላጎታቸውን መነሻ ባደረገ አልጎሪዝም ነው ወይስ በቻይና መንግስት ጣልቃ ገብነት የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም። ለነገሩ ቲክቶክ የቻይናን መንግስት ላለማስቀየም ስለ 1989ኙ እኤአ የታይናሚን አደባባይ ጭፍጨፋ የሚያሳዩ ቪዲዮችን ከገጹ ማውረዱን በአደባባይ አምኗል። ሆኖም በዚህ ውሳኔው ተጸጽቶ አሰራሩን ማሻሻሉን ደጋግሞ ቢገልጽም የፈለገውን ያህል ሰሚ ያገኘ አይመስልም። በነገራችን ላይ ይህ ጭፍጨፋ የቻይናን ኮሚኒስታዊ አገዛዝ በመቃወም ሰልፍ የወጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ወጣቶች ቤጂንግ በሚገኘው የታይናሚን አደባባይ በጦሩ በግፍ የተጨፈጨፉበት መሆኑን ያስታውሷል።

ወደ ቲክቶክ ስንመለስ የምዕራባውያንን አመኔታ ለማግኘት ከፍተኛ ወጭ አውጥቶ የተጠቃሚዎችን መረጃ አሜሪካ በሚገኝ ሰርቨሩ ለብቻ ማስቀመጡንና ከቻይና ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ጓዳውን ከፍቶ ከፈለጋችሁ መጥታችሁ አረጋግጡ ቢልም በጀ ያለው አልተገኘም። አሜሪካና አጋሮቿ ግን ቲክቶክን ሞኝህን ፈልግ። አትድከም። አናምንህም። ይልቅስ በአሜሪካ ያለውን ድርሻህን ሽጠህ ራስህን አድን እያሉት ነው። ቲክቶክ ቢቸግረው ተጠቃሚዎቹን አድኑኝ ሲል ዘመቻ ከፍቷል። ወደ ፍርድ ቤት ለመሔድም እየተሰናዳ ነው። ከዚህ ሁሉ ውዝግብና እሰጥ አገባ በኋላ ቲክቶክ መቀጠል ቢችል ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል። ፈጠራንና ውድድርን ከማበረታታት ባሻገር ዘና ፈታም ያደርጋል ይለናል The Economist። በነገራችን ላይ አሜሪካ ቲክቶክ ላይ ጥርሷን መንከስ የጀመረችው ዛሬ አይደለም።


**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «በጎ ውሳኔ የመልካም በረከቶች ውጤት ነው»

- አቶ ወስን ቢራቱ
የድሬ ፍሬዎች በጎ አድራጎት ድርጅት መስራች



ጽጌረዳ ጫንያለው

### የእናቱ ልጅ

እሱ ልክ እንደ እናቱ ነው፡፡ የተራቡን መጋቢ፤ የተጠማውን አጠጪ፣ የታረዙን አልባሽ፡፡ በዚህ መልካምነቱ ብዞዎች ከስሙ ይልቅ ‹‹ሩህሩሁ ሰው›› ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ ከመንገድ ወድቆ ያየውን ሁሉ ማለፍ እንደማይቻለው ስለሚያውቁ ነው፡፡

እሱ ማለት ስጡኝን አያውቅም፤ ያለውን መስጠት፣ ማካፈል እንጂ፡፡ የቤተሰቡንና የጓደኞቹን ገንዘብም ከአልባሌ ቦታ አይጥልም፡፡ ከዚያ ይልቅ የበረከቱ ተቋዳሽ ይሆኑ ዘንድ በጎ ተግባራትን በመስራት የልባቸውን ሀሴት ይሞላል፡፡

ዛሬ ላይ ይህ ደግ ሰው ብዞዎች የሚሰጡትን ገንዘብ ከራሱ ደምሮ ከ 1500 በላይ ተማሪዎችን በቋሚነት እየመገበ ይገኛል፡፡ በዚህ ተግባሩም በትምህርት ቤት ምገባ ‹‹አምባሳደር›› ለመባል በቅቷል፡፡ ከዚህ ሻገር ሲል እጆቹ ሰፊ ናቸው፡፡ በማረሚያ ቤትና በሆስፒታል ቋሚ ሰራተኞች ቀጥሮ ወጎኖቹን ይንከባከባል፡፡ የዛሬው ‹‹የሕይወት ገጽታ›› አምድ እንግዳችን አቶ ወስን ቢራቱ፡፡

### የእናት ውርስ

ድሬዎች አብዛኞቹን በሚያስብል እውነት መልካምነታቸው የበዛ ነው፡፡ ወስን ደግሞ እንደ ድሬ ልጅነቱ የሚጋራውን ባህሪ አይለቅም፡፡ እሱን ለየት የሚያደርገው ግን መልካምነቱ እጅግ የበዛ መሆኑ ነው። ሁሌም ደግነት መገለጫው ነው፣ ቅንነቱ ይለያል፡፡ ማንንም የሚመርጥ አይደለምና ለሁሉም ደራሽነቱ ይታወቃል፡፡

አቅመ ደካሞች፣ ታራሚዎች፣ ታማሚዎችና ችግረኛ ተማሪዎች የእርሱን እገዛ እስከፈለጉት ‹‹አለሁላችሁ ማለቱን አያቋርጥም፡፡ በእርግጥ ይህንን መልካምነት የወረሰው ከወላጆቹ ነው፡፡ የእነርሱ ቤት ዘወትር ለችገራቸው ሁሉ መጠጊያ፣ መሰብሰቢያ፤ ማደጊያና ወግ ማዕረግን ማሳያ ነው፡፡

ማንም በእዚህ አጸድ የተገኘ ቢኖር ‹‹አንተ ልጅ አይደለህም፣ ይህ አይገባህም›› ተብሎ አያውቅም፡፡ ቤቱን መጠጊያ፣ መጠለያ ያደረገ ሁሉ በቃ! መብቱ የማይጣስ፣ የማይገፋፍ ልጅ ሆኖ ያድጋል፣ ይኖራል፡፡

በቤቱ እስካለ ደግሞ ‹‹ ወንድሜ፣ እህቴ ተብሎ ሊጠራ ግድ ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ ልጅ እናት አባቱ ቢኖሩ እነሱም የቤቱ አባወራና እማወራ ናቸው፡፡ ይህ አይነቱ የቤተሰብ ታሪክ የጀመረው ወስን ገና ሳይወለድ ጀምሮ ነበር። ቤተሰቡ እንደዛሬው የተትረፈረፈ ሀብትና ገንዘብ ሳይኖረው በፊት፡፡

የዛኔ እናት ጉልት ቸርቻሪ፣ አባት ደግሞ ጫማ ሰፊ ነበሩ፡፡

ጥንዶቹ ቤታቸው በሰው ፍቅር የተሞላ ነውና የገቢያቸው ማነስ ታይቷቸው አያውቅም፡፡ መቼም ቢሆን ‹‹አጣን፣ ነጣን ጎደለብን›› አይሉም፡፡ ይህ አይነቱ መልካምነት በድሬዎች አገላለጽ ‹‹ቲከን በሪ›› ወይም ‹‹ በራቸው ለሁሉም ክፍት የሆነ ተብሎ ይተረጎማል። ሁለቱም ከእጃቸው የሚሰስቱት የለም፡፡ ሁሌም ቤታቸው በበረከት ተሞልቶ ከመሶቡ ተርፎ ይነሳል፡፡

ወስን ቤተሰቦቹ ያሳለፉትን ችግር የሚያውቀው ‹‹ነበር›› ተብሎ ሲወራ ነው፡፡ ደግነትን ግን ከልጅነቱ ጀምሮ እያየው አድጓል፡፡ እነሱ ዝናን ያተረፈ ሆቴል ገንብተው ሲያስተዳድሩም መልካምነታቸው አብሮ እንደዘለቀ አረጋግጧል፡፡ በተለይ ደግሞ ሰራተኞችን ሲቀጥሩ የሚከተሉት መስፈርት እጅጉን ያስደንቀዋል፡፡

ሰዎች አይቀጥሯቸውም የተባሉት ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸውን በእነርሱ ቤት ቅድሚያ አግኝተው ሲቀጠሩ ተመልክቷል፡፡ ሴት ልጅ ስንትም ልጅ ይኑራት፤ ነፍሰጡርም ትሁን በእነርሱ ቤት የስራ እድል አታጣም፡፡ ልዩ እንክብካቤም ታገኛለች፡፡ በቤቱ የሰራተኛ ምግብ የሚባል ልዩነት ስለሌለ ከልጅነቱ ምግቡንም ፍቅሩንም በእኩል ተሻምቶ እንዲያድግ ዕድል አግኝቷል፡፡

ወስን በልጅነቱ ከቤተሰቡ በጣም አስቸጋሪ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ ገንዘብ አባካኝና በሱስ የተጠመደ መሆኑን ጭምር አይረሳም፡፡ በቤታቸው እያየ ያደገው መልካምነት ግን እንደገና ሰርቶታል። መልካሙን፣ ሩህሩሁንና ለጋሹን የዛሬውን ወስን ፈጥሯልና፡፡ ያለፈበት አጋጣሚ ማንነቱን ከመልካም ጎዳና እንዲያሳርፍ አስችሎታል፡፡ ዛሬ ለደከሙ፣ ለወደቁ፣ ማረፊያ፣ ለተራቡ፣ ለታረዙ ደራሽ የመሆን ምስጢሩ ይኸው እውነት ነበር፡፡

ለዚህ ማንነት ግን የእናቱ ድርሻ ወደር የለውም፡፡ ‹‹ከእናቴ የወረስኩት ብዙ ነገር አለ፡፡ በተለየ የሕይወት መርህ ሆነውኛል የምላቸው ግን ሁለቱን ነው፡፡ አንደኛው ከሌለኝ ላይ መስጠትን ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በሥራ መለወጥ እንደሚቻል፡፡ ይህንን ደግሞ እንደ መማሪያ መጽሐፍ ሆኖ ያለፈ ታሪኳን እንድናነበው አድርጋናለች፡፡ በየቀኑ እንደተረት በመንገርም ‹‹ይህም ይቻላል እንዴ! እንድንል አስችላናለች፡፡ እናም ለባህርዬ መለወጥ የእርሷ ጠንካራ እጆች ብርታት ሆነውኛል›› ይላል፡፡

ወስን ገንዘብ ለማይሆን ተግባር ሲውል ምን ችግር እንደሚያስከትል ኖሮት ያውቀዋል፡፡ በዚህም ‹‹ቤተሰብ ነጻ ፈቃድ ሲሰጥ ጎን ለጎንም ቁንጠጥ ማድረግና የት ዋለ ማለት ይገባዋል፡፡ ›› ሲል ይመክራል፡፡ እንደ አብነት የሚጠቅሰው ደግሞ ቤተሰቡን ነው፡፡ የዛኔ እርሱ በሆቴላቸው የፈለገውን እያገኘ ጊዜውን ያሳልፋል፡፡ አመኔታ ባይጣልበትም እንደ ኃላፊ ቁጥጥር ያደርግ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሱስ ውስጥ እየገባ ጭምር ሌሎችን እንዲጋብዝ አድርጎታል፡፡ መለስ ብሎ ሲያስበው ግን ባለሀብት ወላጆች ለልጆቻቸው ገንዘብ ከመስጠት ባሻገር እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ማየት ይኖርባቸዋል ሲል ይመክራል፡፡

### የልጆች በረከት

የእነ ወስን ቤተሰብ ሲነሳ ሳይጠቀስ የማይታለፍ አንድ እውነት አለ፡፡ ቤቱ በልጆች ዓለም የተባረከ መሆኑን። የወስን እናት 18 ልጆችን ወልደዋል፡፡ አባቱ ደግሞ ከሌሎች ሁለት ሚስቶች ስምንት ልጆችን ወልደዋል፡፡ በጥቅሉ 26 ልጆች እህትና ወንድም ናቸው፡፡ ከእነዚህ መሀል ወስን 14ኛው ልጅ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ እንዲህ በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁልጊዜ በንግግሩ ‹‹ቤተሰብ የማንነት መሰረት ነው›› ይላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በበዛ ቤተሰብ ውስጥ በልጅነቱ መልካምነትን በጎነትን እንዲያውቅና ከዛሬው መከሊቱ እንዲገናኝ ምክንያት ሆኖታልና፡፡

### ወስንና ትምህርቱ ...

የወስን እናትና አባት ትምህርት በስነምግባር የተቃኘ መሆን እንዳለበት ያምናሉ፡፡ በመሆኑም የሚወዱትን ልጃቸውን ወስንን የቀለም ትምህርቱን እንዲቆጥር ክርስቶስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስገብተውታል፡፡ ትምህርት ቤቱ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የቆየበት ሲሆን፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ ወደ ድሬደዋ አጠቃላይ ትምህርት ቤት በመዘዋወር እንዲከታተል ሆኗል፡፡ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች በስነምግባር የተኮተኮተባቸው ናቸው፡፡ መልካምነቱን ገንብቶ እንዲያድግ አግዘውታል፡፡

በወስን እምነት ሙያዎች ሁሉ በትምህርት መጎልበት አለባቸው፡፡ እሱ ትምህርቱን ከ12ኛ ክፍል ቢያቋርጥም ለተሰማራበት ሙያ የሚሆን ስልጠና ወስዷል፡፡ አሁንም ቢሆን ዘርፉን አሳድግበታለሁ ብሎ ካሰበ መሰልጠን እንደሚፈልግ አጫውተናል፡፡

ወስን ከትምህርት ጋር በተያያዘ የሚለው አለ። ‹‹ዓለማችን በትምህርት፣ በጥበባት፣ ወይም በተወሰኑ ዘርፎች ብቻ የተገደበች አይደለችም፡፡ ከትምህርት ባሻገር ብዙ ዘርፎች ደግፈው ያቆሟት እንጂ›› ሲል ይናገራል፡፡ ይህ አቋሙ ትምህርቱን ከ12ኛ ክፍል አቋርጦ የንግዱን ዓለም እንዲቀላቀል ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ መሆኑ ‹‹የእኔ ድርሻ በንግዱ ዘርፍ ተሰማርቼ ሀገርንና ትውልድን መታደግ ነው›› እንዲል አስችሎታል፡፡

### የሥራ ሕይወት

ወስን ከቤተሰቦቹ ቤት የወጣው ጋብቻን ባሰበ ጊዜ ነው፡፡ ‹‹አሁን የራስህ ጌታ መሆን አለብህ፤ ትዳር መስርት ›› ሲባል ቤተሰቡን ትቶ አባወራነቱን ለማስመስከር ደፋ ቀና ወደማለቱ ገባ፡፡ መጀመሪያ የወሰደው ርምጃ ባለቤቱ የራሷ ሥራ እንዲኖራት ማድረግ ነበር፡፡

በወቅቱ ከአባቷ በተማረችው ሙያ የውበት ሳሎን ከፍታ እንድትሰራ ተገቢውን ዕቃ ገዛላት። ቀጥሎ ደግሞ ለራሱ የሚሰራበትን አመቻቸ፡፡ በስድስት መቶ ብር ደሞዝ ተቀጥሮ ውሎውን ‹‹ሚቶ መናፈሻና በርገር ›› ላይ አደረገ፡፡

መናፈሻው ግዙፍ የሚባል ሲሆን፤ በርካታ ሰራተኞችን በውስጡ አቅፏል፡፡ በቀን 13 ትላልቅ ሙክት አርዶ ደንበኞቹን ያስተናግዳል፡፡ በዚህ ቤት የእርሱ ድርሻ የማስተዳደሩ ተግባር ነበር። እንደ ስራአስኪያጅ ሳይሆን እንደ ባለቤት ሆኖ ይሰራል፡፡. ስራዎችን በሁሉም ቦታ እየገባ የሚያከናውነው እሱ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያት ነበረው፡፡

የመናፈሻው ባለቤት ወይዘሮ ቀለሟ አበበና አቶ ግርማ ወልዴ የነጻነቱ ምንጭ ናቸው፤ ልክ እንደ እናትና አባቱ ድረው ኩለውታል፡፡ ለእነሱ ከተባለ ደከመኝን አያውቅም፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከቀናት በአንዱ እምቢኝ ሲል ከማያሳልፈው የሥራ ዕድል ጋር ተገናኘ፡፡

በወቅቱ ‹‹ቢጂአይ ወይም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ›› ‹‹የሚሊኒየም ፓርክ በአሁኑ አጠራር አሊቢራ ፓርክ››ን ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደር በከፍተኛ ወጪ ሰርቶ ያስረከበበት ግዜ ነበር፡፡ የቦታው ኃላፊ ሆኖ እንዲሰራ አማራጭ ያገኘው ወስን እድሉ ያልጠበቀው በመሆኑ ለውሳኔ እንዲቸገር ሆኖ ነበር፡፡

በተለይ የልብ ወዳጆቹን የቀድሞ አሰሪዎች ትቶ መውጣቱ እጅጉን ሲያጨንቀው ከርሟል፡፡ ምን ብሎ እንደሚናገርም ግራ ሲጋባ ቆይቷል፡፡

የመናፈሻው የመመረቂያው ጊዜና ሥራ የሚጀምርበት ሰዓት በመድረሱ መናገሩ ግድ ነበር። በዚህም ሲፈራ ሲቸር ሁኔታውን ለባለቤቶቹ አሳወቀ። በወቅቱ ሰዎቹ ነገሩን ቀድመው ስለሰሙት ምንም ሊሉት አልወደዱም፡፡ ይልቁንም መልካም እድል ተመኝተው በቸር ሸኙት፡፡ እሱም ስለዚህ ውለታቸው ዘወትር ያመሰግናቸዋል፡፡

ወስን በአዲሱ መናፈሻም የገጠመው መልካም ነገር ብቻ ነበር፡፡ በዚህም እንደለመደው ጠንክሮ ይሰራል። ጊዜው ባይፈትነው ኖሮ ስኬታማ እንደሚሆንበት ያምናል፡፡ ይሁንና ድሬ ችግር ስለገጠማት ገበያውም በዚያው ልክ ወደ መቀዛቀዙ ገባ፡፡ ወስን ሥራውን ሊቀጥል ቢከበደው ጥቂት ለማረፍ ወሰነ፡፡

የወስን እረፍት እስከመጨረሻው አልዘለቀም። በግዜው የአክስታቸው ልጅ ሆቴል ስለሚያስመርቅ ወደ ቡታጅራ ጠራው፡፡ በሆቴሉ ምርቃት ወቅትም እንደለመደው ሁሉም ቦታ ደምቆ ታየበት፡፡ እስከ ቆየበት ጊዜ ለሆቴሉ ባለቤት ጥሩ ገቢ አስገኘ። አካሂዱ ቤተሰቡን ትቶ ስለነበር ከ15 ቀን በላይ አልቆየም፡፡

ወስን ወደ ቤተሰቡ ከተመለሰ በኋላ የተመረቀው ሆቴል እርሱ እንደነበረበት ጊዜ አልሆንልህ አላቸው፡፡ ይህ ሲታወቅ በልመና እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ለስድስት ወር ያህል የአስተዳደሩን ቦታ ሸፍኖ በጥሩ ሥራ ሆቴሉን ወደ ቀደሞ ክብሩ መለሰው፡፡ ወስን ረጅሙን ጊዜ ከቤተሰቡ ተለይቶ በማሳለፉ ከዚህ በላይ በዚያ መቆየት አልተቻለውም፡፡ ቤተሰቡን፤ የልጅነት ጥሪውን ትቶ ቡታጅራን የሙጥኝ ማለት አልሆነለትም፡፡ ዳግም ወደ ትውልድ ቀዬው ድሬደዋ ተመለሰ፡፡

ድሬደዋ እንደገባ ጊዜ ሳይፈጅ የምግብ ዝግጅት ሥራውን ጀመረ፡፡ ለምግብ መስሪያ የሚሆኑ እቃዎችን በማሟላት ተለያዩ ተቋማትና ዝግጅቶች ብፌ አዘጋጅቶ ማቅረብን ለመደ፡፡ ሰርግ፣ ክርስትና፤ ልደትና ቁርባን ልዩ ልዩ በዓላትና ፕሮግራሞች በእርሱ መድመቅ ጀመሩ፡፡ የምግብ መገልገያ እቃዎቹን ለኪራይ አገልግሎት ጭምር በማዋል ጥቅም አገኘ፡፡

ወስን ገቢውን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ተግባራት አሉት፡፡ አንዱ ፋሚሊ ወተትን ከቤተሰቡ በመረከብ በድሬደዋና ሐረር ዙሪያ ማከፋፍል ነው፡፡ ሰርግን በመምራት ዝግጅቱን ማድመቅንም ተክኖታል ውሃን ጨምሮ የለስላሳ መጠጦችን የማከፋፈል ተግባር ይከውናል፡፡ የእንቁላልና ዳቦ ማከፋፈል ሥራም ሌላው የገቢ ምንጬ ነው፡፡ በተለይ የዳቦ ጉዳይ ሲነሳ የእሱ መሰረት የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር እንደሆነ ያነሳል፡፡

የወቅቱ ምክትል ከንቲባ የአሁኑ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር ‹‹የድሬ ፍሬዎች በጎ አድራጎት ድርጅት›› ከተመሰረተ በኋላ ሥራውን ስላዩ 200 ሺህ ብር እንዲሰጠው ታስቦ ነበር፤ ሆኖም ገንዘቡ ጠፊ ነውና 100 ሺህ ብር ተሰጥቶት፡ በቀሪው የዳቦ ማሽን ይገዛለት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «በጎ ውሳኔ የመልካም...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ



ተብሎ ተወሰነ፡፡

እርሱ ግን በጊዜው ተናዶ እንደነበር ። አሁን ላይ ሆኖ ሲያስበው ግን ውለታ እንደዋሉለት ያምናል፡፡ ምክንያቱም እንዲያ በመሆኑ ዛሬ ብዙዎችን መመገብ ችሏል፤ የራሱን የገቢ ምንጭም አሳድጓል፡፡

ወስን ከገንዘብ ጋር ተያይዞ የሚያራምደው የተለየ አቋም አለ፡፡ ይህም «ገንዘብ ባንክ መቀመጥ የለበትም፤ ማህበረሰቡን እያገለገለ መዟዟር አለበት » የሚል ነው። እርሱም የሚያደርገው ይህንኑ ነው፡፡ እንዲያውም ከዚህ አቋሙ አንጻር በቅርቡ የሰርግ ዲኮር ላይ በስፋት ለመሳተፍ አስቧል፡፡ ለዚህ ደግሞ እህቱ በባለቤትነት የምትመራው «ላሊዛ ዲኮር» እንደሚያግዘው ነግሮናል፡፡

### የድሬ ፍሬዎች

«መልካም ነገር ሁሉ ከፈጣሪ፣ መጥፎ ነገር ሁሉ ደግሞ ከሰይጣን እንዳልሆነ አስተውል፡፡ ምክንያቱም ፈጣሪ መጥፎን ወደ መልካም የመቀየር ብቃት አለው። ሰይጣንም ያጠፋህ ዘንድ መልካም የሚመስል ነገር ሊያዘጋጅልህ ይችላል። እናም ሁልጊዜ መልካም ማሰብና መልካም መሆን መልካም ነገር እንዲገጥምህ ማመቻቸት ነው፣ መጥፎዎችን ማራቅም ነው፡፡ መጥፎ ደግሞ ለአንተም ሆነ ለሰዎች ጉዳት እንጅ ጥቅም የለውም» የወስን የሁልጊዜ መመሪያ ነው፡፡

ይህ መመሪያውም ትናንት ላይ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በጎ ተግባርን ሲከውን እንዲቆይ አስችሎት ዛሬ ላይ ይዞት የቀጠለውን «የድሬ ፍሬዎች በጎ አድራጎት ድርጅት»ን እንዲመሰርት አግዞታል፡፡ ይህ የሆነውም ከ2012 ዓ.ም በኋላ ነበር፡፡ ከዚህ ዓመት ጀምሮ በዓላት ከትናንቱ ይልቅ ትልቅ ትርጉም የሚሰጣቸው ሆነዋል፡፡ የጎዳና ልጆችን በእናትና አባቱ ቤት ሰብስቦ የሚመግብበት፤ በዓልን ማክበር የማይችሉ አቅመ ደካሞችን ደስተኛ የሚያደርግበት፤ ሆስፒታሎች አካባቢ እየሄደ የቻለውን የሚያደርግበት ልዩ እለታት ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘወትር ጓደኞቹ ከጎኑ ናቸው፡፡ በተለይም የ06 ወጣት አመራሮች ለእርሱ በጎ ተግባር ትልቅ አስተዋፅጾ ነበራቸው፡፡ በስራው የተደሰቱ አንዳንድ ድርጅቶችም ቢሆኑ ከስሩ አልተለዩም።

ቤተሰቦቹም ቢሆኑ ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው፡፡ እንደዛሬው ችግረኞችን ማብላት፤ ማጠጣት፣ ለተማሪዎች ዩኒፎርም ማሰፋት፤ የአቅመ ደካሞችን ቤት መጠገንና መሰል ተግባራትን መከወን ባልተለመደበት ወቅት ወስን ለብዙዎች መድረስ እንዲችል አግዘውታል፡፡ ሆኖም በዓላትን ብቻ ተጠቅሞ ለሰዎች መድረስ ለእርሱ እርካታን አልሰጠውም፡፡ በተለይም ሰፈራቸው ትምህርት ቤት ተከፍቶ የማይመገበውን ተማሪ ቁጥር ሲመለከት «የምሰራው ተግባር በቂ አይደለም» እንዲል አስችሎታል። ነገር ግን ስራውን ዘላቂ ለማድረግ ቋሚ ገቢ የግድ ነው። እናም የእያንዳንዱን ሰው ቤት ማንኳኳት ጀመረ፡፡ የዛኔ ብዙዎች ተስፋ አስቆራጭ መልስ ይሰጡት ነበር። እሱ ግን ድርጅቱን እስኪመሰርት የተለያዩ ድጋፎችን ማድረጉን ቀጠለ፡፡

የድጋፉ መጀመሪያ 2007 ዓ.ም ሆነ፡፡ ሰፈራቸው በተከፈተው ሕዳሴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሚማሩና ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ላሉ ውስን ተማሪዎች በመድረስ፡፡ በቻለው ልክ በሰበሰበው ገንዘብ ዩኒፎርም በማሰፋትና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶችን በመግዛት እስከ 2008 ዓ.ም ዘልቋል፡፡ ቀጥሎም በጣም ችግረኛ የሆኑ ከ300 እስከ 400 የሚደርሱ ተማሪዎች እንዳሉ ሰማና እነርሱን ለማገዝ ፈጠነ፡፡ በ2010 ዓ.ም ደግሞ ሕልሙን እውን የምታደርግለት የባለቤቱ የአክስት ልጅ ወይዘሮ ወጋየሁ ኃይሉ ተገኘች፡፡

ውጭ ሀገር የምትኖር ሲሆን፤ በየአራት ወሩ አንድ ሺህ ዶላር ቃል ገብታ ትልክለታለች፡፡ በዚህም ከተማ አስተዳደሩ የመለመላቸውን 120 ተማሪዎች ሙሉ ምገባ እንዲያገኙ አደረገ፡፡ ቀጠለናም ሀጅ አሕመድ አክሰዴ በሚባሉ ባለሀብት ስም የተመሰረተ በጣም ችግረኛ ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ነበረና ወደዚያ በማቅናት በአብዱልአዚዝ ከሪም አጋዥነት የ100 ተማሪዎችን ምግብ እንዲቻል ሆነ፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ ዋች ኤንድ ፐሪር ኢን ሚኒስትሪስ ድርጅትንና ቤተሰቦቹን ከጎኑ በማድረግ በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች 15 ትምህርት ቤቶችን ይዞ በአማካኝ 100 ተማሪዎችን በድምሩ ከ1500 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች ደረሰ፡፡

በዋናነትን የገቢ ምንጩ ቤተሰቡ ቢሆንም ከእነርሱ ባሻገርም የእናቱ እህት ወይዘሮ አበራሽ ወንድሙና በአሜሪካ እና በአውሮፓ የሚገኙት የአቶ አሰፋ ወልደ ጻዲቅ ልጆች እንዲሁም በአዲስ አበባ የምትገኘው አክስቱ ወይዘሮ እመቤት ወንድሙና ባለቤቷ አቶ ማስረሻ ስዩም ሳይጠቀሱ የማያልፉ አጋዦቹ ናቸው፡፡ ለዚህም ሁሉንም አጋዦቹን በተማሪዎቹ ስም ከልብ ያመሰግናል፡፡

ወስን በትምህርት ቤት ምገባ ብቻ ሳይወሰን በትምህርት ቤት እድሳትም ላይ ተሳታፊ ነው፡፡ የሕዳሴ ትምህርት ቤትን የተወሰኑ ክፍሎች ከቤተሰቡ በሰበሰበው ገንዘብ ሙሉ እድሳት አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ የመማሪያ ክፍሎችን ሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል በሆስፒታሎች ውስጥም በቋሚነት በየዓመቱ ዕለተ ስቅለት ላይ ሕሙማንን ይመግባል፡፡ በትልቁ ድሬደዋ ሪፈራል ሆስፒታልም በቋሚነት ሁለት ሰራተኞችን ቀጥሮ ሕሙማን ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ተንከባካቢ ለሌላቸው ሕሙማን አጃ፣ ወተት፣ ዳይፐርም ያቀርባል፡፡

ወስን ለድሬደዋ ማረሚያ ቤትም ለሴቶችና ሕጻናት ማቆያ ሙሉ ግብዓት አሟልቶ በቋሚነት ሞግዚት ቀጥሮ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡ አሁንም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለታራሚ ልጆች ያቀርባል፡፡ የወስን ተግባር ይህ ብቻም አይደለም፡፡ በወር አንዴ ከየክልሉ የመጡ ግን መኖሪያቸውን ጎዳና ያደረጉ ወገኖችን ቁርስ የመመገብ ፕሮግራም ያከናውናል፡፡ ከታመሙ መድሀኒት እንዲገዛላቸውም ያደርጋል፤ ወደ ሀገራቸው መመለስ ከፈለጉም እንዲሁ ሙሉ ወጪያቸውን ሸፍኖ ይሸኛል፡፡

### ፈተናዎች...

ወስን በበጎ ሥራው ላይ ፈተና አላጣውም፡፡ በብዙ አጋጣሚዎች ተፈትኗል፡፡ በማብሰያ ቦታ ጥበት፤ በማጓጓዣ መኪና፣ በነዳጅ፣ በመብራት መጥፋትና በሌሎችም ችግሮች መሀል ተመላልሷል፡፡ ለዚህ ደግሞ አጋዥ አካላት እንደሚያስፈልጉት ያምናል፡፡ አብሮ በመስራት በረከቱ እንዳለ ሆኖ ሀገርን ከፍ ማድረጉ ላይ አስተዋጽኦው ላቅ ያለ በመሆኑ፡፡

የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር በአንዳንድ ጉዳዮች እንደሚያግዛቸው ቃል ገብቶለታል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ለሌሎች ለመድረስ ብዙ ጎዶሎዎችን የሚሞላ አካል ያሻቸዋል፡፡ «ወገኖቻችን የእኛ ግዴታዎች ናቸውና ኑ አብረን እንስራ፣ እንደግፋቸው» ሲልም ጥሪ ያቀርባል፡፡

### ቀጣዩ እቅድ

የወስን የቀጣይ እቅድ በጎነቱን መጨመር ብቻ ነው። ወደፊት ኑሮ ቢወደድም በበጎነት የሚተርፈው ብዙ ነውና ሰባት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በአማካኝ 100 ተማሪዎችን በማከል 2200 ተማሪዎችን መድረስ ይፈልጋል፡፡ ይህ እውነት ደግሞ የነፍሱ ጥሪ ነው፡፡

በአካባቢው ሆስፒታል የሚገቡ እናቶች ቁጥር በየጊዜው ይጨምራል፡፡ በዚህ ምክንያትም እናቶች ከወለዱ በኋላ በሆስፒታል የሚቆዩት ቢበዛ ለሦስት ቀናት ብቻ ነው፡፡ ይህ ችግር የገባው ወስን እነዚህ ሴቶች ሜዳ እንዳይወድቁ የሚያስችል ተግባር ለማከናወን አስቧል፡፡ይህን ሀሳብ የሚከውነው ደግሞ ግቢ ተከራይቶ አስር ክፍሎችን በማዘጋጀት ይሆናል፡፡

**በጎነት ውሳኔን ይፈልጋል። ከተረፈ ላይ ሳይሆን ካለ ላይ መስጠትንም ይጠይቃል፡፡ በጎ ማድረግን ሁሉም ሲመኘው ይችላል፡፡ እንዲያም ሆኖ ቁርጥ ውሳኔ የግድ ይላል**

ወስን በዚህ ቤት ባህሉን በጠበቀ መልኩ እናቶች በወጉ እንዲታረሱ ይፈልጋል፡፡ የእርሱ ሀሳብ ቢያንስ ሦስት ወር የሚታረሱበትን እድል መስጠትና ከዚሁ ጎን የሙያ ስልጠና እንደዲያገኙ ማገዝ ነው፡፡ ከስፍራው ከወጡ በኋላም ሥራ እስኪያገኙ ለሦስት ወራት ቤት ተከራይቶ ሊንከባከባቸው ዕቅድ ይዟል፡፡

### ቤተሰብ

ረጅም ዓመታትን በእጮኝነት አሳልፈዋል ከዛሬዋ ባለቤቱ ወይዘሮ አይናለም ማሞ ጋር፡፡ እርሷ ጥሩ የውበት ባለሙያ ነች፡፡ እርሱ ደግሞ በልምድም ቢሆን ጎበዝ ሼፍና ነጋዴ፡፡ የእርሷ የሙያ መሰረት አባቷ ናቸው፤ ታዋቂ የውበት ሳሎን አላቸው፡፡ የሁለቱ መጣመር ይፋ ሊሆን ሲቃረብ ወስን ከቤተሰብ ቤት መውጣት ግድ አለውና የራሱ ጌታ ሊሆን በብዙ ደከመ፡፡ ድካሙ ግን በከንቱ አልቀረም፡፡ ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ማኖር ቻለ፡፡

አሁን አባወራነቱ ለልጁ ብቻ ሳይሆን ለ1500 ተማሪዎች ጭምር ተርፏል፡፡

ዛሬ ለ20 ሕጻናትና በሆስፒታል ለተኙ አቅመ ደካሞች አባት ነው፡፡ ይህንን ያረጋገጠው ደግሞ ገና ሲሞሸር ጀምሮ ነበር፡፡ የእርሱ ሰርግ ድምቀቱ ችግረኞቹ ነበሩ። የጎጆው መሰረቶችም ሆነዋል፡፡ ድግሱን አድምቀው ጋብቻውን ቀድሰውለታል፡፡ በሰርጉ ታድመው በረከትን ሸልመውታል፡፡ በእነርሱ ስም ኬክ አሰርተው ቆርሰዋል። «ትዳርህ ይባረክ ሲሉም መርቀውታል፡፡ ምርቃታቸው ደርሶም አንድ ሆና በአስተሳሰቧ ሺህ የሆነች፤ የተባረከች ልጅን እንዲያገኝ ሆኗል፡፡

### መልዕክት

በጎነት ውሳኔን ይፈልጋል፡፡ ከተረፈ ላይ ሳይሆን ካለ ላይ መስጠትንም ይጠይቃል፡፡ በጎ ማድረግን ሁሉም ሊመኘው ይችላል፡፡ እንዲያም ሆኖ ቁርጥ ውሳኔ የግድ ይላል፡፡ አንዳንዴ ላለመስጠት፣ ከእጅ ላለማውጣት ምክንያት ይደረደርበታል፡፡ ሀብታም ስሆን፤ ሲኖረኝ፤ እግዚያብሔር ሲሰጠኝ. ወዘተ የሚሉ የስስት ሀሳቦች በአዕምሮ ውል ይላሉ፡፡ እናም የእኛ ሰው መስጠት የኖረበት ባህሉ ቢሆንም ይህ አይነቱ ሰበብ ወደኋላ ይጎትተዋልና ማካፈልን ከጎደለን፤ ከሌለን ነገራችን ላይ እናድርገው፤ በውሳኔም እንደግፈው፡፡ የዚህ ጊዜ ፈጣሪ በረከቱን ያድለናል» ሲል ወስን ይመክራል፡፡

«በጎ ውሳኔ መቼም ቢሆን አያስቆጭም፡፡ ይልቁንም መልካም በረከቶችን ይዞ ይመጣል» የሚለው በጎ አድራጊ፤ በጎ ውሳኔ የመልካም በረከቶች ውጤት ስለመሆኑ ይናገራል፡፡ ለዚህ እንደማሳያ የሚጠቁመው ማኅበረሰቡን ነው፡፡ ወስን እንደሚለው «ማኅበረሰቡ በመስጠት ልምዱ ችግር እንኳን ሲያጋጥም ተቋቁሞ ማለፍን ያውቅበታል፡፡ ከእርሱ እጅ ያለው ጥሪት ለራሱ ብቻ የሚበቃው ሆኖ ሳለ ለሌሎች መትረፍን ልምዱ አድርጎታል፡፡ አሰጣጡ ዘላቂነት እንዲኖረው ግን ይህን ልምድ የሚያዳብርበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ችግረኞችን በቋሚነት እንዲያግዝም በወጉ በመቀናጀት የተወሰኑ ሰዎችን መያዝ ይቻላልና፡፡ ይህ ዕቅድ ደግሞ በተግባር ሊሰራበት ይገባል፡፡»፡ ሲል አቶ ወስን መልዕክቱን ያስተላልፋል፡፡

# የከተማ ሥነ ሕንፃ ቅርሶች በምን መስፈርት ይመዘገባሉ?

**ዳግም ከበደ**

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ከተማ ማደስና ቅርስ እንክብካቤ ዙሪያ እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች ላይ መግለጫ መስጠቱ ይታወሳል፡፡ በመግለጫው የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ቀደም ሲል በአዲስ አበባ የቅርስ መስፈርት ያላሟሉ ሁሉ ቅርስ ተብለው ተመዝግበው እንደነበር ገልጸው ነበር፡፡

ዓለም አቀፍ የቅርስ ምዝገባን መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት አንድ ሕንፃ የተገነባበት ዘመን፣ ውጫዊ እና ውስጣዊ ዲዛይኑ፣ ኪነ-ሕንፃው፣ ታሪካዊ ዳራው፣ እና ሌሎች መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ በቅርስነት እንደሚመዘገብና ጥበቃና እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው አብራርተዋል፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም ይህንን ጉዳይ በዛሬው አምዳችን ላይ ለመዳሰስ ወዷል።

የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር እንደሚሉት፤ የመሥሪያ ቤቱ አንደኛው ተግባር በሀገሪቱ የሚገኙ ቋሚ፣ ተንቀሳቃሽ ሆነ የማይዳሰሱ ቅርሶችን የመመዘገብ ሥራ ነው። እነዚህን ኃላፊነቶች የሚያከናውነው የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 209/1992 መሠረት በመቋቋሙና በዚህ አዋጅ መሠረት ቅርስን የመመዝገብ ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ፣ በቅርሶች ላይ ምርምር እንዲሁም የማልማት ተግባርና ተልዕኮ ስለተሰጠው ነው። ሌላው አዋጅ ቁጥር 839/2006 ደግሞ ቅርሶችን በብሔራዊና በክልል ደረጃ የመመደብ ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል።

‹‹ቅርሶችን የምንመዘግበው በአዋጁ መሠረት በተሰጠን ተግባርና ኃላፊነት በመመሪያ ቁጥር 9/2006 መሠረት ነው›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በመመሪያው በወጣው መስፈርት አማካኝነት እስከ ዛሬ ድረስ ቅርሶችን ሲመዘግብ መቆየቱን ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ‹‹ቅርስ ምንድነው?›› የሚለውን ጉዳይ ለማስገንዘብ በመመሪያው መሠረት ለክልሎች ሥልጠና እንደሚሰጥ ያስረዳሉ። ይህንን ተከተሎም ክልሎች በየራሳቸው ምዝገባ እንደሚያደርጉ ይናገራሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ ቀደም ሲል ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የመመሪያ ቁጥር 9/2006 በ2015 ዓ.ም እንዲሻሻል መደረጉን ይገልፃሉ። ለመሻሻሉ ምክንያት የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱን በድጋሚ በማዋቀር ሂደት ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ለማውጣት መሆኑን ይገልፃሉ። ማንኛውም ቅርስ እሴት ሊኖረው እንደሚገባ በመግለጽም በምዝገባ ሂደት ላይ ያንን የእሴት መስፈርት እንዲጠበቅ፣ አስፈላጊው ምርምርና እንክብካቤ ለማድረግ መሆኑን ያስረዳሉ።

‹‹አዲስ አበባ ላይ ብዙ ቅርሶች አሉ›› የሚሉት የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር፤ ሀውልቶች፣ ታሪካዊ አደባባዮች፣ ከእምነት ተቋማት ጋር የሚያያዙ ቅርሶች፣ በየተቋማቱ አገልግሎት የሚሰጡ ቅርሶች መኖራቸውን ይናገራሉ። በቅርቡ ግን በስፋት በማህበረሰቡ ዘንድ አወዛጋቢ ጉዳዮች የተነሱበት የሥነ ሕንፃ ቅርስ የሚባለው መሆኑን ይናገራሉ።

የተሻሻለው መመሪያ የከተማ ሥነ ሕንፃን በጥቅሉ እንደሚያስቀምጥ የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰሩ ይሁን እንጂ በዝርዝር በመከፋፈል እንደማያስቀምጥ ያስረዳሉ። በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች የዓለም ክፍሎች አጨቃጫቂ የሆነው ጉዳይ ‹‹ከተሞች የልማት ማዕከል ስለሆኑና በየጊዜው እየለሙ ስለሚሄዱ ከተማ ላይ ያለ የሥነ ሕንፃ መስፈርት ማውጣት ነው›› የሚለው ዋነኛው ጉዳይ መሆኑን ያነሳሉ። በመሆኑም ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ ላይ ‹‹ቅርስ ማለት የሰው ልጅ በፈጠራ፣ በሳይንስ፣ በባህል ያካበተው፣ የሠራውና ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ያለበት ነው›› የሚል ቢሆንም በጥቅሉ ከሥነ ሕንፃ ቅርስ ጋር ተያይዞ በዝርዝር ጉዳዩን የማይገልፅና የሚያወዛግብ መሆኑን ይናገራሉ።

> **የከተማ ሥነ ሕንፃን በሚመለከት ከባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት በመነሳት ቅርሶችን ለመመዝገብ፣ ውሳኔ ለሚሹት እልባት ለመስጠት በሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የመጠበቅ የማልማትና የመንከባከብ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ**

በዚህ ምክንያት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ይህንን ጉዳይ መመልከት መጀመሩን ይገልፃሉ። በዚህም ‹‹የከተማ ሥነ ሕንፃ ቅርስ ማለት ምንድን ነው›› የሚለውን ዝርዝር መስፈርት በማውጣት መመራት እንደሚያስፈልግ ድምዳሜ ላይ መደረሱን ይናገራሉ። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያትም ከልማት ሥራዎች ጋር ተያይዞ ተደጋጋሚ አጨቃጫቂ ጉዳዮች በመነሳታቸው መሆኑን ያስረዳሉ። አንዳንዶቹ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ድረስ የደረሱ በመሆናቸውና ምክንያት መሰል ችግሮች ወደፊትም እንዳይከሰቱ እልባት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንደሆነ ይገልፃሉ። ከዚህ በኋላም ቅርሶች የከተማ ሥነ ሕንፃ ቅርሶች በጥቅል ሳይሆን በተመዘነ መስፈርት እንዲመዘገቡ የሚያደርግ አሠራር መዘርጋቱን ይናገራሉ።

የከተማ ሥነ ሕንፃ ቅርስ አመዘጋገብ ዝርዝር መስፈርት ስናዘጋጅ የሶስት ሀገራትን ተሞክሮ ወስደናል የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ የሲዊዘርላንድ፣ ጃፓንና የካናዳን የአመዘጋገብ ሂደትና መስፈርቶችን እንደ መነሻ እንደተጠቀሙ ይናገራሉ። ዓለም አቀፍ የቅርስ አመዘጋገብ መስፈርቶችን በቀጥታ፣ ከሌሎች ሀገራት የተወሰዱትን ደግሞ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሃቅ ጋር ለማጣጣምና ለመውሰድ እንደተሞከረ ይናገራሉ።

ከዚህ መነሻ የከተማ ሥነ ሕንፃ የሚባሉትን ለመለየት ከ100 የሚመዘን መስፈርት መኖሩን የሚገልፁት ዳይሬክተሩ፤ ይህም በአምስት እንደሚከፈል ይናገራሉ። የመጀመሪያው ሥነ ሕንፃው ሲሆን፤ አንድን ከተማ ከተማ የሚያሰኘው፣ ውበት የሚሰጠውና ታሪክን መናገር የሚችለው እራሱ ሕንፃው (በሥነ ሕንፃ ውበት፣ ዘይቤው፣ አገነባቡ፣ እድሜው፣ አርክቴክቱ፣ ዲዛይኑ፣ ውጫዊ ገፅታው፣ ውስጣዊ ገፅታው) የሚናገረው ነገር መሆኑን ያስረዳሉ። በመሆኑም የመጀመሪያው መስፈርት ሥነ ሕንፃው ላይ እንደሚያተኩር እና በአጠቃላይም 30 ነጥቦችን እንደሚይዝ ያስረዳሉ።

ሁለተኛው ክፍል የሕንፃው ታሪክ መሆኑን የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ታሪክ ሲባል ሶስት ጉዳዮችን የያዘ መሆኑን ይገልፃሉ። የመጀመሪያው ከግለሰብ ጋር የሚያያዝ ታሪክ (በሀገሪቱ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ተፅእኖ ፈጣሪ፣ ጉልህ ድርሻ ያበረከተ) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሁነት መሆኑን ነው ያስረዱት። ‹‹በሥነ ሕንፃው ውስጥ ቀደም ባሉ ጊዜያት ምን ተካሂዶበታል›› የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ መሆኑን ያስረዳሉ። በሶስተኛነት በታሪክ ንዑስ መስፈርት ውስጥ የሚቀመጠው ጉዳይ ዳራው መሆኑን ያስረዳሉ። ይህ መስፈርትም ሥነ ሕንፃው በቀጥታ ከየትኛው የታሪክ ክፍል ጋር እንደሚገናኝ የሚያስረዳ መሆኑ መታወቅ እንዳለበት ይገልፃሉ።

ይህ የሥነ ሕንፃ ታሪኩን የሚያብራራው ክፍል በጥቅሉ 30 ነጥቦችን የያዘ ሲሆን፤ አንድ መቶ ነጥብ ከሚይዙት አምስቱ መስፈርቶች ውስጥ ሶስተኛው ጉዳይ ሥነ ሕንፃው ያለበት ከባቢያዊ ሁኔታ እንደሆነ የሚያስረዱት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ቀደም ሲል የነበሩት ታሪኩ፣ ሥነ ሕንፃው እሴቱን ጠብቆ እንደቀጠለ የሚረጋገጥበት መስፈርት መሆኑን ይናገራሉ። ሌላው ሥነ ሕንፃው ለመልከዓ ከተማው የሚያሳየው ነገር መኖሩ፣ የገዘፈና እንደ ምልክት (landmark) የሚጠቀስ መሆኑና ይህም በአጠቃላይ አስር ነጥቦችን የያዘ መሆኑን ይገልጻሉ።

በተጨማሪም ሕንፃው የሚሰጠው አገልግሎት፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ግልጋሎቶች፣ ለሌሎች ግልጋሎቶች መዋል መቻሉ እንዲሁም በጥገና ወቅት የሚኖረው ወጪና ሌሎች ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ጉዳዮች መስፈርቶች መሆናቸውን ይናገራሉ። ይህም በጥቅል ተደምሮ 20 ነጥቦችን እንደሚይዝ ይገልፃሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ በሥነ ሕንፃ ቅርስ ምዝገባ ሂደት በመጨረሻ መስፈርትነት የሚቀመጠው በቅርስ ቋንቋ ኢንተግሪቲ እየተባለ የሚቀመጠው መሆኑን ይናገራሉ፤ ይህም ማለት ሥነ ሕንፃው አሁን ያለበት ሁኔታና እሴትነቱ ምን ላይ እንደሆነ፣ ቀደም ባሉት ጥገናዎች የነበረውን እሴት ጠብቆ ስለመቆየቱ የሚረጋገጥበት እና አሁንም ድረስ ያለበት ሁኔታን የሚታይበት መስፈርት መሆኑን ይናገራሉ። በዚህ መስፈርትም አስር ነጥቦች እንደሚሰጡና በአጠቃላይ ከመቶ ድምር የሕንፃው በቅርስ የመመዝገብና ያለመመዝገብ ውሳኔ የሚረጋገጥበት እንደሆነ ይናገራሉ።

በተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 9/2015 መሠረት ‹‹አንድ ሕንፃ የከተማ ሥነ ሕንፃ ቅርስ ነው›› የሚባለው ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘት ሲችል እንደሆነ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ይናገራሉ። ይህም ለሁለት እንደሚከፈልና ደረጃ (ሀ) እና ደረጃ (ለ) ተብለው እንደሚቀመጡ ይናገራሉ። ደረጃ (ሀ) ላይ የሚቀመጡት ሥነ ሕንፃዎች ከ65-100 ውጤት የሚያመጡት ሲሆኑ ምንም ቅያሬ የማይደረግባቸው፣ የውጭ ገፅታቸው እንዳለ የሚጠበቁ መሆኑን ያስረዳሉ። በደረጃ (ለ) ውስጥ የሚመደቡት ደግሞ ከ50 እስከ 64 ውጤት የሚያገኙት እንደሆነ ይናገራሉ። እነዚህም እንደሚጠበቁ ነገር ግን እንደየሁኔታቸው ማሻሻያ ሊደረግባቸው እንደሚችል ያስረዳሉ። በተለይ በእርጅናና በልዩ ልዩ ምክንያት ማሻሻል ሲፈለግ በፈጠራ ውጤቶች ጥገና እንደሚደረግባቸው ይናገራሉ።

‹‹ከ49 እና ከዚያ በታች የምዘና ውጤት ያመጣ ሥነ ሕንፃ እንደ ቅርስ አይቆጠርም›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው፤ በመሠረታዊነት አብዛኛዎቹ የዓለማችን ሀገራት ይህንን አካሄድ እንደሚከተሉ ይናገራሉ። ኢትዮጵያም በሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ መስፈርቶችን በማስቀመጥ ልየታና ምዝገባ እንደሚደረግ ያስረዳሉ።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተጨማሪነት አጨቃጫቂ የሆኑ ሥነ ሕንፃዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ የባለሙያዎች ቡድን እንዲቋቋም ማድረጉን ይናገራሉ። ሥነ ሕንፃዎቹ በቅርስነት እንዲመዘገቡ አሊያም እንዳይመዘገቡ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ተጠቅመው የሚመዝኑ ሶስት ባለሙያዎች መኖራቸውንም ይናገራሉ። ባለሙያዎቹ ምዘናውን ሰርተው ሲያመጡ መረጃው ተቀባይነት ካገኘ ወዲያው ውሳኔ እንደሚሰጥበትም ይገልፃሉ። አወዛጋቢ ነገር የሚያስነሳ ከሆነ ደግሞ በቅርስ ምዝገባ ጉዳይ በሚደረጉ ስብሰባዎችና በማኔጅመንት ምክክር ውሳኔ እንደሚሰጥበት ይገልፃሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የሥነ ሕንፃ ቅርስ ምዝገባ ሂደትን ለማፋጠን ከወረቀት ሥራ በመውጣት በቴክኖሎጂ ለመታገዝ እየተሠራ መሆኑንም ይናገራሉ። ይህም ቅርሶች ሲመዘገቡ በዲጂታላይዜሽን መስፈርቶቹን ሕንፃዎቹንና አጠቃላይ መረጃዎችን በመመዝገብ ለማስቀመጥ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የኮሪደር ልማቱን አስመልክቶ በሚነሱ ሕንፃዎች አማካኝነት የአራዳ ፒያሳ እና የፍልውሃ አካባቢን መውሰድ እንደሚቻል የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ 147 ቤቶች በቅርስነት ተመዝግበው እንደነበር ያነሳሉ። በመሆኑም ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ለእነዚህ ቅርስ ተብለው ለተለያዩ ሥነ ሕንፃዎች ቅድሚያ ሰጥቶ መገምገሙን ይገልፃሉ። ያም ሆኖ ከአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ኪነጥበብ ቢሮ ከፍተኛ ባለሙያዎችና አመራሮች ጋር በመሆን የመስክ ጉብኝት መደረጉን ይገልፃሉ። በዚህም ዋና ዋና የሚባሉትን ቅርሶች የመጠበቅና የማልማት ሥራ እንዲሠራ መወሰኑን ይናገራሉ። ቀሪዎቹ በመመሪያው መሠረት መስፈርቱን የማያሟሉት፣ ቀድሞ የነበራቸውን እሴት የቀየሩት፣ ወደ ንግድ የተቀየሩትን፣ ከስም ጋር ብቻ የተያያዙና ከሥነ ሕንፃ ውበትና ጥራት ጋር ያሉት ላይ ደግሞ ውሳኔ እንደተሰጠባቸው አስረድተዋል።

በመጨረሻም የከተማ ሥነ ሕንፃን በሚመለከት ከባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት በመነሳት ቅርሶችን ለመመዝገብ፣ ውሳኔ የሚሹትን እልባት ለመስጠት የሀገር ውስጥንና ዓለም አቀፍ መስፈርቶች ተመስርቶ የመጠበቅ የማልማትና የመንከባከብ ሥራዎችን እየሠሩ እንደሚገኙ ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ተናግረዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ አስጀማሪው ጀግና

**ዋለልኝ አየለ**



በሆቴሎች፣ ካፌዎች፣ በተቋማት እና በሌሎች ቦታዎች የኢትዮጵያ መሪዎች ፎቶ ተሰቅሎ እናያለን። ሁሉም ማለት በሚያስችል ሁኔታ የሚጀመሩት ከአጼ ቴዎድሮስ ነው፡፡ ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ እስከ ወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ ድረስ ይታያሉ፡፡ የአጼ ቴዎድሮስ ልክ እንደ መነሻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያን መሪዎች በፎቶ የማወቅ ጥያቄ ቢጠየቅ አብዛኛው ሰው የሚያውቀው ከአጼ ቴዎድሮስ በኋላ ያሉትን ነው፡፡

የታሪክ ምሁራን እና ፖለቲከኞች ስለኢትዮጵያ ታሪክ እና የፖለቲካ ሁኔታ ሲያወሩ ብዙ ጊዜ መነሻቸውን የሚያደርጉት ከአጼ ቴዎድሮስ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት፣ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እንደሚጀምር ተደርጎ ይነገራል፡፡ የዚህ ምክንያቱ የታሪክ ሰው ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ዘርፍ ላይ ያሉ ሰዎች እንደሚያውቁት አጼ ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ተበታትና የነበረችዋን ኢትዮጵያን አንድ በማድረጋቸው ነው፡፡ በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 156 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ራሳቸውን የሰውትን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን እናስታውሳለን፡፡

ነገሩ በአጭሩ እንዲህ ይጀምራል፡፡ የፋሲካ ማግሥት ዕለት መቅደላ አምባ ላይ የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት እና በሎርድ ኔፒዬር የተመራው የእንግሊዝ ሠራዊት ጦርነት ገጥመው ድሉ የእንግሊዞች ሆነ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች እጅ ከመውደቅ እራሳቸውን ማጥፋትን መርጠው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ፡፡ ቀብራቸውም በመቅደላ መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ፡፡ የዚህን ጀግና ታሪክና ሥራዎች ዘርዘር አድርገን እናስታውሳለን፡፡

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የጀግና ምሳሌ ናቸው፡፡ የቆራጥነትና ወኔ ማሳያ ናቸው፡፡ ስለጀግንነትና ቆራጥነት ሲነሳ በአጼ ቴዎድሮስ ይመስላል፡፡

የታሪክ ባለሙያዎችና ምሁራን የሚሉት አንድ ነገር አለ፡፡ አጼ ቴዎድሮስ የጦር ጀግና ብቻ አልነበሩም። ዘመናዊነትንና ሥልጣኔን የሚመኙ ባለራዕይ ነበሩ፡፡ በነገራችን ላይ ለዚህ መታሰቢያ የደበረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ጋፋት ኢንዱስትሪ በሚል የቴክኖሎጂ ንቅናቄ ጀምሮ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ በየጊዜው ውይይቶችንም ያዘጋጃል፡፡ ከአራት ዓመታት በፊት ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው አንድ የውይይት መድረክ ላይ ተሳታፊ ነበርኩ፡፡ ብዙ ምሁራን ሲያነሱ የነበረው አጼ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ራዕይ የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ ንባብና ሥልጣኔን ያስተዋውቁ ነበር፡፡ አብዛኛው ታሪካቸው ግን የሚታወቀው ከጦር ጀግንነት ጋር የተያያዘው ነው። የዚያን ዘመን ባህሪ ስለነበር ነው፡፡ አጼ ቴዎድሮስ ግን ከዘመን ቀድመው ቴክኖሎጂን የተመኙ ነበሩ፡፡

ስለ አጼ ቴዎድሮስ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተመራማሪዎች በተለያየ ጊዜ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እነዚህ የታሪክ ጸሐፊዎች የአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆኑ የውጭ አገራት ጸሐፊዎች ጭምር ናቸው። ጥቂቶችን መጠቃቀስ እንችላለን፡፡

**ፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ**

‹‹ቴዎድሮስ የዘመናዊ ሥልጣኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር።»

**ቮልድማየር፡**

‹‹ቴዎድሮስ፣ ኃይልና ታላቅነት ሳያንሰው፣ የምቾትና የቅምጥል ኑሮ የማያታልለው እንዲህ ያለ ንጉሥ ከቶ የት ይገኛል? የሁላችንም እምነት እግዚአብሔር ኃይሉን የለገሠው የሕዝቡንም ቁሣዊና መንፈሣዊ ደኅንነት ለማረጋገጥ የታጨ መሣሪያ መሆኑ ነው።»

በባህሩ ዘውዴ የታሪክ መጽሐፍ ላይ እንደተገኘው መረጃ፤ ቴዎድሮስ ለአገራቸው ዕውቀት መስፋፋት የነበራቸውን ጉጉት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ በማለት ነበር የገለጹት።

(1) ጥር 1858፣«የኢትዮጵያ ሰዎች ድንቁርናታችን ዕውርነታችን ሳይሰሙት አይቀርም።»

(2) መጋቢት 1858፣ « አሁንም እኔ የምፈልገው ዕውር ነኝና ዓይኔ እንዲበራ ጥበብ ነው።»

(3) ሚያዝያ 1858፣ « የኢትዮጵያ ሰዎች ዕውር ነኝ፤ ዓይናችንን ያበሩልን፤ እግዚአብሔር በሰማይ ያብራልዎ!»

(4) ሚያዝያ 1859፣ «ከብት አለመፈለጌ ከብር ሆኜ አይደለም፤ ዕውር አህያ ነኝና ለጥበብ ዓይኔን ትከፍቱልኝ ብየ ነው እንጂ፣ በእግዚአብሔር ኃይል፤»

ከእነዚህ ደብዳቤዎች አንድ ነገር እንረዳለን፡፡ ይኸውም አጼ ቴዎድሮስ ለእውቀት ሽግግር የነበራቸውን ከፍተኛ ፍላጎት፡፡ ለአገሪቱ ዘመናዊነት ያደረጉት ጥረት እዚህ ላይ ግልጽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለእርሳቸው የተጻፉ አንዳንድ መጻሕፍት እንደሚሉትም አጼ ቴዎድሮስ ከራሳቸው በላይ ለሌላው ያስባሉ፡፡ የግል ሕይወታቸው አያሳስባቸውም፡፡ ከአገር ውስጥ የታሪክ ጸሐፊዎችም ተክለጻድቅ መኩሪያ እንዲህ ብለው ነበር። « ቴዎድሮስ፣ ሞትን የናቁ፣ ድሎትን የራቁ» ናቸው ሲሉ ይገልጿቸዋል።

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ታስረው ከነበሩት እንግሊዛውያን ውስጥ አንዱ የነበረው ዶክተር ሔንሪ ብላንክ ስለአፄ ቴዎድሮስ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

‹‹ለመጀመሪያ ግዜ በ1852 ዓ.ም አፄ ቴዎድሮስን ሳገኛቸው ዕድሜያቸው 48 ይሆን ነበር! በሰላም ግዜ ለስላሳ ሆነው ደስ የሚያሰኙ በተቆጡ ግዜ ደግሞ በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡና የሚያሸብሩ እሳተ ገሞራ የሚወረውሩ ነበሩ! በድንገት ሲቆጡ መላ አካላቸው የሰውን ልጅ ከፍ ካለ ድንጋጤ ላይ ይጥላል! ጠይሙ ገላቸው ሲኮሰኩስ ... ስሱ ከንፈራቸው ሲንቀሳቀስና ፀጉራቸው ሲዘናፈል በጠቅላላ ሰውነታቸው የአንበሳነት ፀባይ የያዘ አስደንጋጭ ይሆናል!››

አፄ ቴዎድሮስ የንግሥና ስያሜያቸው ቴዎድሮስ እንዲሆን የመረጡት ‹‹ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ሲነግስ ኢትዮጵያን እስከ ባሕር ያሰፋታል፤ ፍርድና አስተዳደርንም ያስተካክላል›› የሚባል ትንቢት ስለነበር ሕዝቡ ‹‹ይህ ትንቢት የእርስዎ ነው›› እያሉ አሞካሿቸው። ‹‹ስሜን ቴዎድሮስ በሉ›› ብለው እንዳወጁ ታሪካቸውን ጽፎ በ1985 ያሳተመው ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ይነግረናል።

ጳውሎስ ‹‹ቴዎድሮስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ?›› የሚለውን ጥያቄ በመፅሐፍ አንስቶ ‹‹ሁሉንም ጠባይ አሟልተው የያዙ ሰው ነበሩ። ይህም ማለት ደግ ናቸው፣ ክፉም ናቸው፣ ሩህሩህ ናቸው፣ ጨካኝም ናቸው፣ ፍርድ አዋቂ ናቸው፣ ፍርድ ገምድልም ናቸው›› ሲል ማስረጃ እያጣቀሰ ይገልፃቸዋል።

እስኪ የአፄ ቴዎድሮስን ፍርዶች እንመለከትና በዘመኑ የነበረውን የፍትህ ስርዓት በመጠኑ እንቃኝ። አጼ ቴዎድሮስ በሰጧቸው ፍርዶች መነሻነትም በትንቢት ተነግሮላቸዋል። እንደተባለው ፍርድና አስተዳደርን በማስተካከል ረገድ ምን ያህል ተሳክቶላቸው ነበር የሚለውን የራሳችንን ግንዛቤ እንይዛለን። ፍርዶቹ አንዳንዶቹ አስገራሚ፣ አንዳንዶቹ አሳዛኝና አስደንጋጭ አንዳንዶቹም አስተማሪ ናቸው።

### የጋይንቱ ችሎት

አፄ ቴዎድሮስ ጎንደር ጋይንት ላይ ሰፍረው ስለ ወታደሮቻቸው በአርሶ አደሩ ላይ ተሰሪ አገቡአቸው። ተሰሪ ማግባት ማለት አርሶ አደሩ ወታደሮቹን እንዲቀልብ በየቤቱ መመደብ ማለት ነው። በወቅቱ የተደራጀ ጦር ሰራዊትና ለጦር ሰራዊቱ የሚመደብ የመንግሥት ባጀት ስላልነበር የነገስታቱ ጦር በየደረሰበት ያለው ሕዝብ እንዲቀልበው ይታዘዝ ነበር። ከእነኚህ የጋይንት እና የአካባቢው አርሶ አደር እንዲቀልባቸው ከታዘዘላቸው የቴዎድሮስ ወታደሮች መካከል አንዱ ወታደር አንዱን አርሶ አደር ገደለው። የሟች ዘመዶች ለአፄ ቴዎድሮስ አመለከቱ። አፄውም ወታደሮቻቸውን አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን እንዲጠቁሙ አዘዙ። ሆኖም ወታደሮቹ በሙሉ በአንድ ላይ አድመው ገዳዩን አናውቅም ብለው በቄስ እየተገዘቱ ስለወጡ ገዳዩ ሊታወቅ አልቻለም።

ቴዎድሮስ ገዳዩን ወታደር ለማወቅ የተደረገው ሙከራ ባለመሳካቱ ተናደው ‹‹ወታደር ብላ! ባላገር አብላ! ያልኩ እኔ ነኝ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል›› ብለው ተነስተው ለከሳሽ ነገሩት። ከሳሽም ምኑ ሞኝ ‹‹እኔ ንጉስ መግደል አይቻለኝም›› አለ። ቴዎድሮስ እንግዲያውስ ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም ብለው ለሟች ወገኖች የደም ካሳ ገንዘብ ከፍለው አሰናበቷቸው።

### የንጉሱ ትዕዛዝ

ቴዎድሮስ ለአንድ ታማኝ ወታደራቸው ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፈው ‹‹በፈርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳን ብትሆን እንዳታልፍ ጠንክረህ ጠብቅ›› አሉት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ሌላውን ወታደራቸውን ጠርተው ‹‹ፈረስ እያለዋወጥክ ይህን ወረቀት የጁ አድርሰህ በስድስት ቀን ውስጥ በአስቸኳይ ተመለስ›› ብለው አዘዙ። መልዕክተኛው ወታደር መልዕክቱን ለማድረስ ፈርቃ በር በሚባለው ቦታ ማለፍ ግድ ሆነበት። ፈረሱን እየጋለበ ፈርቃ በር ደረሰ። አስቀድሞ ማንንም እንዳያሳልፍ የታዘዘው የፈርቃ በር ዘበኛም የንጉሱን መልዕክት እንዳያልፍ ከለከለው።

መልዕክተኛው ‹‹ከንጉሡ በስድስት ቀን የጁ ደርሼ እንድመለስ በአስቸኳይ ተልኬ ነው ልለፍ›› አለው።

የፈረቃ በር ጠባቂም ‹‹ከንጉሥ ከተላከ አትከልክሉት ይለፍ የሚል በማህተም የተደገፈ የይለፍ ደብዳቤ ካለህ አሳየኝ እና አሳልፍሃለሁ ካልሆነ ግን እኔም የንጉሥ ትዕዛዝ ስላለብኝ አታልፍም›› ሲል መለሰለት።

መልዕክተኛው ወታደርም የንጉሥ ትዕዛዝ ሆኖበት በግድ አልፋለሁ ብሎ መንገድ ሲጀምር ጠባቂው ወታደር በጥይት ተኩሶ ገደለው።

የሟቹ መልዕክተኛ ወገኖችም ጉዳዩን ከሰሱና ለፍርድ አፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ። በችሎት የተቀመጡት ፈራጆች ሁሉ ገዳይ ላይ ፈረዱ ‹‹እምቢ አልፋለሁ ቢልህ ለንጉሥ ማመልከት ሲኖርብህ እንዴት የንጉሥ መልዕክተኛ ትገላለህ! ለጥፋትህ ሞት ይገባሃል›› ሲሉ ፈረዱበት።

አንድ አስተዋይ ፈራጅ ከተቀመጡበት ተነስተው ‹‹መታየት የሚገባው ከንጉሡ የተሰጠው ትዕዛዝ ነው። ንጉሡ የፈርቃ በር ጠባቂን ጠርተው ያለኔ ፈቃድ እርጉዝ ሴት እንኳን እንዳታልፍ ብለው አዘዙ። መልዕክተኛውን ደግሞ በአስቸኳይ የጁ ደርሶ እንዲመጣ በማዘዛቸው በዚያ በፈርቃ በር በኩል ማለፍ ነበረበት። ስለዚህ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሥ ነገስቱን ነው። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ›› ብለው ተቀመጡ።

እዚህ ጋር እንግዲህ በዚያ ዘመን የነበረውን ንጉሥ የሚያስተች ዲሞክራሲ ሳናደንቅ አናልፍም። የአስተዋዩ ፈራጅ ንግግር ብቻ ሳይሆን የንጉሡም ምላሽ የሚደንቅ ነው።

አፄው ምን አሉ መሰላችሁ! ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ‹‹እንዲህ ነው መሸምገል፣ ሁለት ጠጉር ማብቀል›› ብለው የአስተዋዩን ፈራጅ ፍርድ ካደነቁ በኋላ ‹‹በደለኛው እኔ ነኝ ፍረዱብኝ›› ብለው በተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ። ከዛም ፈራጆች በሰጡት ፍርድ መሰረት ለሟች ወገኖች 500 ብር የደም ካሳ እንዲከፍሉ አፄ ቴዎደሮስ ላይ ፈረዱና ጉዳዩ በዚህ ተቋጨ።

የአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ ለታሪክ ቅርብ በመሆኑ ሰዎች ብቻ የሚታወቅ አይደለም፡፡ የሕዝብ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፤ ስለአጼ ቴዎድሮስ የተገጠሙ የለቅሶ እና የውደሳ ግጥሞች የሕዝብ ስነ ቃል እስከሚመስሉ ድረስ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ። በእርግጥ የሕዝብ ናቸው፤ ምክንያቱም በሕይወት ዘመናቸው ያወደሳቸውም፣ የሰደባቸውም ሕዝብ ነው። ሲሞቱ ያለቀሰላቸውም ሕዝብ ነው፡፡

እዚህ ላይ አስገራሚው ነገር ያ አስፈሪ ጀግና አጼ ቴዎድሮስ ይሰደቡ ነበር፡፡ አንዱን ብቻ እንጥቀስ።፡ አባቷን እና ወንድሟን በአጼ ቴዎድሮስ የተገደለባት አልቃሽ እንዲህ ብላለች፡፡

**አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ**
**አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ**
**ይህንን ሲሰማ ያንራል ለአመሉ**
**ማናትም ካላችሁ «ምንትዋብ ናት!»በሉ!**

እንዲህ ያለችዋ ሴትዮ እንዳልተገደለችና ይልቁንም በእኔ ሞታ ዝናን ለማግኘት ነው ብለው አጼ ቴዎድሮስ እንደተናገሩ ተክለጻድቅ መኩሪያ ጽፈዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ከደጃች ጎሹ ጋር በነበራቸው የጉራምባ ጦርነት ላይ አንድ አዝማሪ አቋሙን ቀይሮ አጼ ቴዎድሮስን ለማወደስ የሚሞክር ግጥም ገጥሞ ‹‹እንዲህ አይነት አስመሳይና ወላዋይ አይጠቅምም›› ብለው አስገድለውታል፡፡ አዝማሪው መጀመሪያ ከደጃች ጎሹ ጎን ሆኖ እንዲህ አለ።

**ያንዛብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሳ**
**ወርደህ ጥመድበት ከሸንብራው ማሳ**

ወዲያውኑ ድል ለአጼ ቴዎድሮስ ሆነች፡፡ የደጃች ጎሹ ጦር ተሸነፈ፡፡ ይህ አዝማሪ ጉዱ ፈላ፡፡ ያሸነፈውን እያወደሰ መኖር ፈለገ፡፡ ወዲያውም እንዲህ አለ፡፡

**አወይ የአምላክ ቁጣ**
**አወይ የእግዜር ቁጣ**
**ሰው ወዳጁን ያማል የሚሰራው ሲያጣ**
**ዱሳ ይገባዋል የአዝማሪ ቀልማጣ**

በማለት አጼ ቴዎድሮስ ወዳጄ ናቸው አለ፡፡ ንጉሡ ግን እንዲህ አይነት ከሃዲ ወዳጅ የለኝም ብለው ‹‹ዱላ ይገባኛል›› ሲል ግዴለም ጥይት ይሁንልህ ተባለ፡፡

የአጼ ቴዎድሮስ ነገር ጳውሎስ ኞኞ እንዳለው ነው፡፡ ደግ ናቸው፣ ክፉም ናቸው፣ ሩህሩህ ናቸው፣ ጨካኝም ናቸው፡፡ ከወኔ እና ጀግንነታቸው በተጨማሪ ለሥልጣኔና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ጥረት ያላቸው ባለራዕይ ነበሩ፡፡ ካሳ ኃይሉ (በንግሥና ስማቸው ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ) እነሆ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አስጀማሪ ሆነው በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የኢትዮጵያ ሙዚቃ አብዮተኛ!

**ቤዛ እሸቱ**



ሙሉቀን መለሰ ፤

ይህችን ምድር በ1946 ዓ.ም በቀድሞው ጎጃም ክፍለ ሀገር፣ አነደድ ወረዳ፣ ዳማ ኪዳነ ምህረት መንደር ሲቀላቀል ሀገር፣ መንደር፣ ቀዬው፣ ቤቱም ሰላም ነው፡፡ የሚያምር ልጅነት ነበረው፤ አባቱ ቄስ ታምር ጥሩነህ ልጃቸው እንደሳቸው መንፈሳዊ እንዲሆን በማሰብ ይመስላል ዘወትር ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ ከመዝሙረ ዳዊታቸው ጋር ከእጃቸው የማይነጥሉት ተወዳጅ ልጃቸው ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል መጠነኛም ቢሆን አቋቋሙንም ሆነ ከበሮ አመታቱን ቀስሟል፡፡ ከቤቱ አራት እህትና ሦስት ወንድሞች አሉት፣ ዓለሙ ሙሉ ናት፡፡

የሥሙ ነገር ጂጂ "ሥም የለኝም በቤቴ" እንዳለችው ነው፡፡ ዋና መጠሪያ ሆኖ ከሕዝብ ጋር የተዋወቀበትን "ሙሉቀን" ያወጣችለት እህቱ ስትሆን፣ ወላጅ እናቱ ወይዘሮ እናትነሽ ጌታሁን ደግሞ "ሙሉሰው" ትለው ነበር፡፡ የዚህ ምክንያቱ እሱን ከመውለዳቸው በፊት አስወርደዉቸው ስለነበር፤ እንዲሁም፣ ከሱ በላይ ያሉት አራት ታላላቆቹን ሲወልዱ በከባድ ምጥ ስለነበርና ሙሉቀን ሲወለድ በቀላል ምጥ መገላገላቸውን ተከትሎ ሙሉሰው አሉት፡፡ አባት በሌላ ወገን ቀይ፣ ድንቡሽቡሽ ልጃቸውን "ሥማቸው" ይሉታል፤ በመሬት የተነሳ ሙግት ቢጤ ገጥሞ ነበርና ከሳሾችህን ሥማቸው ሲሉት ነበር፡፡ ከዚህ ሁሉ ስያሜ የእህቱ ስያሜ ጎልቶ ሙሉቀን የሚለው ገኖ ዋና መጠሪያው ሆኖ ጸደቀ፡፡

በልጅነት እድሜው ከምንም በላይ የሚወዳቸው እናቱ ወይዘሮ እናትነሽ በለጋ እድሜው መሞታቸውን ተከትሎ ሕይወት በእነ ሙሉቀን ቤት እንደቀድሞ በሰላም ልትቀጥል አልቻለችም፡፡ በዚህ መከፋት ውስጥ እንዳለ አጎቱ መለሰ ገሰሰ ሊጠይቋቸው መኖሪያቸውን ካደረጉበት አዲስ አበባ ወደ እነ ሙሉቀን መንደር ዘለቁ፡፡ በወቅቱ ከገጠር ልጅ ላሳደግ ብሎ መውሰድ የተለመደ ነበርና አጎቱ በቤቱ ካሉት ስምንት ልጆች ሙሉቀንን መርጠው "እኔ አሳድገዋለሁ" ብለው ወደ ከተማ ወሰዱት፡፡ መኖሪያው አዲስ አበባ፣ ኮልፌ ሰፈር ሆነ። እንደመንደሩ ሕፃናትም ትምህርት ቤት ተመዘገበ። ታዲያ አጎቱ እንዲማርበት በገዙለት ደብተር ላይ "ሙሉቀን መለሰ" ብለው አጎትየው ጻፉ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሙሉቀን መለሰ በሚለው ፀና።

ከአጎቱ ጋር ኑሮውን ቢገፋም የአጎቱ ቤት ኑሮ ብዙም የሚያወላዳ አልሆነለትም፡፡ በተለይ ከአጎቱ ሚስት ጋር መስማማት ከብዶታል፡፡ በዚህ መከፋት ውስጥ እያለ ኮልፌ አጠና ተራ የአባት ጡረተኞችና ወላጅ ያጡ ሕፃናትን የሚቀበል ድርጅት መኖሩን ሰማ፡፡ አላንገራገረም፤ ሄዶ ይቀበሉት ዘንድ ጠየቀ። ጥያቄው ተቀባይነት አገኘ። በተለይ የማሳደጊያው አስተዳዳሪ ተወዳጅ ልጅ ነበር፤ ኤልቪስ የሚል ቅጽል ስም አውጥተውለት ነበር፡፡ ወጣ ሲሉ ልብስ ይዘውለት ይመጡ ነበር፡፡ ወደፊትም ወደውጭ ሀገር ልከው እንደሚያስተምሩት ቃል ገብተውለት ነበር። እዛው ማሳደጊያ ውስጥ የሙዚቃ ትምህርት ቤት መከፈቱን ተከትሎ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ሙዚቃ መማር ጀመረ።ለስድስት ወር ያህል እንደተማረ የእህቱን መታመም ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት አቀና፡፡

ከጎጃም መልስ የሙዚቃ ትምህርቱን አልቀ ጠለበትም። ይልቁንስ በሻይ ቤት ተቀጥሮ እራሱ ለእራሱ ለመኖር መፍጨርጨር ቀጠለ፡፡ አንድ ቀን የጎረምሶች አብሮ ማምሸት የተለመደ ነውና ሙሉቀን ከእኩያ ጓደኞቹ ጋር ሳይታወቃቸው በጨዋታ መሃል የሰዓቱን መምሸት ልብ ሳይሉት ይቆያሉ፡፡ ሳያስቡት ሰዓቱ ሄዶ ነበርና አንዱ ጓደኛቸውን ለመሸኘት ወደ ዳጃች ውቤ ያቀናሉ፤ በዚህ የምሽት ጉዞ የውቤ በረሃ መብራቶች ማርከውታል፡፡ በተለይ ለጓደኛሞቹ የአንደኛው ቤት ውበት ከሌሎቹ የተለየ የውቦች ውብ ሆኖባቸዋል፡፡ "ምንድነው?" ብለው ሲያጣሩ ፈጣን ኦርኬስትራዎች የሚጫወቱበት ፓትሪስ ሉሙምባ የምሽት ክበብ መሆኑ ይነገራቸዋል፡፡ ሲያጣሩ የቤቱ ባለቤት ወይዘሮ አሰገደች አላምረው መሆናቸውን ይደርሱበታል፡፡ "ሥራ ይስጡኝ ብል እሺ ይሉኛል?" ሲል በቅርብ ያለን ባለሱቅ ቢጠይቅ "ጻፍና ጠይቃቸው" ሲል ወረቀትና እስክሪብቶ ሰጠው፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ወደ ውስጥ ገብቶ የጻፈውን ደብዳቤ ለኦርኬስትራ መሪው ሰጠ፡፡

የኦርኬስትራው መሪ ከትንሽዬ ልጅ የተሰጠው ደብዳቤ ያሳቀው ከመሆኑም በላይ ነገሩን ብዙም ከቁም ነገር አልወሰደውም ነበር፡፡ ሁኔታውን ከርቀት የተከታተሉት የቤቱ ባለቤት "ምንድነው?" ሲሉ ጠየቁ። የባንዱ አስተባባሪ በሳቅ ታጅቦ ባለ ደብዳቤው ትንሽዬ ልጅ ፈተና ፈትነውት ካለፈ እንዲቀጥሩት መጠየቁን በሳቅ ታጅቦ ነገራቸው፡፡ ወይዘሮ አሰለፈች "ፈትነውና እየው፤ ካለፈ ይገባል፤ ካልሆነ ሌላ ሥራ እሰጠዋለሁ" አሉ፡፡ በወቅቱ ሙሉቀን በኋላ እንደሚገልጸው በሁሉ ነገሩ ጥላሁንን ለማስመሰል የሚሞክርበት ዘመን ነውና በባዶ እግሩና በቁምጣ ሆኖ "ለእውነት እሞታለሁ፣ አልሳሳም ለነፍሴ" እና "እንክርዳድ እንክርድድ" የተሰኙትን የጥላሁንን ዘፈኖች አቀነቀነ፡፡ በብቃቱ የተማረኩት የምሽት ቤቱ ሠራተኞች የዛኑ ማታ መዋጮ አዋጡለት፡፡ በነጋታው ካኪ ልብስ ተገዛለት። ሱፍ ተለካ፣ ጫማ ተገዝቶለት ተጫማ፡፡ በቤቱ ባለቤት ወይዘሮ አሰለፈችና በሕፃኑ ሙሉቀን መሃል ውል ታሰረ፡፡ ውሉ ሙሉቀን ማታ ማታ በቤታቸው ሊዘፍን፤ እሳቸው በወር 90 ብር ደመወዝ ሊከፍሉት ነው፡፡ በወቅቱ 90 ብር ብዙ ነበርና እሱም "ሚልየነር የሆንኩ መሰለኝ" በማለት በአንድ ወቅት በ1973 ዓ.ም ከደራሲ ስብሀት ገብረእግዚአብሔር ጋር በጻደይ መጽሔት ላይ በነበረው ቃለመጠይቅ ተናግሮ ነበር፡፡

ውብ መልኩ፣ ማራኪ ድምጹ፣ ቅልጥፍናው ታክሎበት የምሽት ቤቱን ሕይወት ለመደ፡፡ በለጋ እድሜው በምሽት ክበቡ አድማጭ የሚይዝ ሆነ፡፡ ያም ቢሆን ብዙ አልዘለቀም፡፡ የፖሊስ ኦርኬስትራ አባላት ዓይናቸውን ጣሉበት፡፡ ገና በቅጡ 16 ዓመት ሳይሞላው ፓትሪስ ሉሙምባ ምሽት ክበብ ውስጥ ከሚጫወትበት ፈጣን ኦርኬስትራ አስኮብልለው የፖሊስ ኦርኬስትራን ተቀላቀለ፡፡ በወቅቱ የኦርኬስትራው ትንሹ ሙዚቀኛ ነበርና በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ነበር፡፡ ኦርኬስትራውን በተቀላቀለበት ወቅት ተወዳጆቹ ደራሲዎች ሰለሞን ተሰማ "የዘላለም እንቅልፍ" የተሰኘ ሥራ፤ ጋሽ ተስፋዬ አበበ "ያ ልጅነት"፣ "እናቴ ስትወልደኝ መች አማካረችኝ"፣ "እምቧይ ሎሚ መስሎ" የተሰኙና ሌሎች ሥራዎችን ለሱ አስበው፤ ግጥምና ዜማ ሠርተውለት በግሩም ሁኔታ ተጫወታቸው፡፡

ምንም እንኳን የራሱን ሙዚቃ መጫወቱና ከኦርኬስትራው ጋር በርካታ ቦታዎች ተዘዋውሮ በመሥራቱ ዝናው ቢናኝም ከፖሊስ ኦርኬስትራ በገዛ ፈቃዱ በመልቀቅ በግል ባንዶች ተዘዋውሮ ሠርቷል። ከዚህ ውስጥ ረዥም ጊዜ በዳህላክ ባንድ ቆይታ ቢያደርግም ከኢትዮ ስታር ባንድ፣ ከኢኪዌተርስ ባንድ፣ ከሮሃ ባንድ፣ እንዲሁም ከሙላቱ አስታጥቄ ጋር ሠርቷል፡፡ ከኦርኬስትራው ከተለያየ በኋላ "የዘላለም እንቅልፍ" እና "ያላየነው የለም" የሚሉ ዘፈኖቹን በሸክላ አስቀርጾ ለአድማጭ በመድረሳቸው ዝናው ይበልጥ ናኘ፡፡ ሙሉቀን ከሠራቸው ተወዳጅ ዘፈኖች መሃል "ሆዴ ነው ጠላትሽ"፣ "ሰውነቷ"፣ "መውደዴን ወደድኩት"፣ "ይረገም ይህ ልቤ"፣ "ውቢት"፣ "ወተቴ ማሬ"፣ "ምነው ከረፈደ"፣ "ናኑ ናኑ ነይ"፣ "ተነሽ ከልቤ ላይ"፣ "ውሃ ወላዋይ" የሚሉት ሥራዎቹ ከሌሎቹ በተለየ በበርካታ አድማጮች ዘንድ የሚታወሱ ሥራዎቹ ናቸው፡፡

ከሠራቸው በርካታ ሙዚቃዎች ውስጥ በሙዚቃ ጥራት ሰውነቷና ሆዴ ነው ጠላትሽ በአሰራር ደግሞ ሙላቱ አስታጥቄ ያቀናበራቸውና ከዳህላክ ባንድ ጋር የዘፈናቸው ቼ በለውና ውቢት የተሰኙት ሥራዎች ከሌሎች ሥራዎች ይልቁበታል፡፡ ለሙሉቀን ዘፈኖች አሁን ድረስ መወደድ በተፈጥሮ የታደለው ተሰጥኦ እንዳለ ሆኖ፤ ዜማና ግጥም ሲመርጥ የሚያደርገው ጥንቃቄ፣ ለሙዚቃ ቅንብር የሚሰጠው ትኩረትና ከባለሙያዎቹ ጋር ተናቦ መሥራቱ የሥራው ጥራት ላይ ይታያሉ፡፡ (በነገራችን ላይ ሙሉቀን ድራምን ጨምሮ ሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሳምሮ ይጫወታል፣ በብዙ ድምፃውያን ሥራ ላይም ድራመር ሆኖ ሰርቷል)። እሱ ሙዚቃን በቃኝ ካላት 37 ዓመታትን ቢሻገርም አሁን ድረስ በበርካታ የሀገራችን የሙዚቃ ወዳጆች ዘንድ የድምጻዊያን ቁንጮ ቦታነትን እንደተቆናጠጠ ዘልቋል፡፡ እሱ ሙዚቃን ከተሰናበተ በኋላ የተወለዱ በርካቶች የሚሰሙት ደግሞም የሚያዜሙት ተወዳጅ ድምጻዊ ነው፡፡

እሱ ጋ ሙዚቃን ለመሥራት ጥድፊያ የለም። ከተለያዩ ደራሲዎች የሚሰጠውን ግጥምና ዜማ ለመምረጥ ጊዜ ይወስዳል፤ በየሄደበት ሰዓት ሰጥቶ ይሰማል፤ በዚህ ሂደት የማይሆነውን ይጥላል፤ ማሻሻል የሚፈልገውን ዜማና ግጥም ያሻሽላል፡፡ አንዱን ከአንዱ ቀላቅሎ የተሻለ ግጥምና ዜማ ያዘጋጃል፡፡ በዚህ የተነሳ የሱ ሥራዎች አሁን ድረስ በልዩነት ይወደዳሉ፡፡ በአንድ ወቅት ሁለገብ የኪነ-ጥበብ ባለሙያ የሆነችውና ለሙሉቀንም በርካታ ግጥሞችን የሰጠችው ዓለምፀሐይ ወዳጆ በሙዚቃው ዘርፍ በሀገራችን በግጥምና ዜማ ረገድ ይፈጸም የነበረውን አነስተኛ ክፍያ ያሻሻለና የግጥምና ዜማ ደራሲዎች የተሻለ ክፍያ እንዲያገኙ ያስደረገ ድምጻዊ መሆኑን መስክራለች፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ሙዚቃን ወደፊት ያራመደ በመሆኑ በበርካታ የሙዚቃ ባለሙያዎች ‹‹የኢትዮጵያ ሙዚቃ አብዮተኛ›› ተደርጎ እንዲታይ አድርጎታል፡፡

ሙሉቀን በተወዳጅ የሙዚቃ ሥራዎቹ አሁን ድረስ ሥሙ ቢነሳም ዓለማዊ ሙዚቃን የሠራው ግን ለ17 ዓመታት ብቻ ነው፡፡ ከዛ በኋላ ዓለማዊ ሙዚቃ በቃኝ ብሎ የመንፈሳዊውን ዓለም ተቀላቅሎ በዝማሬ ከ37 ዓመታት በላይ አገልግሏል፡፡ ሆኖም አሁንም ሙዚቃዎቹ እንደ አዲስ የሚያጣጥሙ ትውልዶች መፈጠራቸውን አላቆሙም፡፡ ሙሉቀን ከሙዚቃው ዓለም የተለየበት ወቅት በዝና ማማ ጫፍ የነካበት፣ የተሻለ ተከፋይ የሆነበትና በየቦታው ፈላጊው የበዛበት ወቅት በመሆኑ ማንም ይህ ይመጣል ብሎ ስላልጠበቀም በሙዚቃ ሥራው የሚወዱት በርካቶችን ያሳዘነ ውሳኔ ነበር፡፡

በበፊት ሕይወቱ ብዙም አማኝ አልነበረም፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያቱን ሲያስረዳ ከችግሩ ያመልጥና በአቋራጭ ሀብታም ይሆን ዘንድ ፈጣሪውን ተማምኖ ሎተሪ ይገዛል፤ ለፈጣሪውም ሎተሪው እንዲደርሰው አደራ ይለዋል፡፡ ግን ሎተሪው ሳይደርሰው ይቀራል። ያኔ ታዲያ ፈጣሪን ተማምኖ ከመማጸን "ፈጣሪ የለም" ወደ ማለት ይሸጋገራል፡፡ ሎተሪውም ሳይደርሰው፤ እሱም ከፈጣሪው ጋር እንደተኳረፈ ኑሮ ይቀጥላል፡፡ ሙሉቀንም በሙዚቃ ሥራው የተሻለ ዝናም፣ ብርም ያገኛል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከሙዚቃ ልምምድ መልስ የተወሰኑ የባንዱ አባላት ወደ "ቸርች" ሲሄዱ አብሬያችሁ እሄዳለሁ በማለት ያቀናል፡፡ በወቅቱ ፈጣሪ የለም ብሎ ይከራከራቸው ስለነበር ግር ቢሰኙም፤ ከፈለገ ይምጣ በማለት አብሮአቸው ይጓዝ ዘንድ ፈቀዱ፡፡ ወደ ቸርች የጀመረው ምልልስ ዘፈን እየሠራ፣ ያለማቋረጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በጸሎት ፕሮግራሞች መካፈሉን ቀጠለ፡፡ በሂደትም ከመጠጥና ከሲጋራ ጋር የነበረው ቁርኝት ተፋታ፡፡

የዘመኑ ተወዳጅ ድምጻዊ ነውና በርካታ ታዋቂ ሰዎችና ባለሥልጣናት የሱን ቤት ለመዝናናት ይመርጡት ነበር። እሱም እንግዳ ለማስተናገድ ይሆነው ዘንድ የእንግዶቹን ምርጫ ታሳቢ ያደረጉ የመጠጥ ዓይነቶች በቤቱ አዘጋጅቶ እንግዶቹን ይጠብቅ ነበር፡፡ ያኔ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ይበልጥ ሲጠጋ እንግዶችን በመጠጥ ከማስተናገድ መቆጠብ ጀመረ፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት ከሙዚቃ ሳይለያይ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ተስቦና ከሱስ ነፃ ሆኖ ወደ ስድስት ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሃል ለሙዚቃ ሥራ ወደ አሜሪካ አቀና፡፡ በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ተዘዋውሮ የሙዚቃ ሥራውን አቀረበ፡፡ ከአንድ ዓመት ከግማሽ የአሜሪካ የሙዚቃ ሥራ ቆይታ በኋላ "ከዛሬ ጀምሮ ከሙዚቃ ሥራ አሰናብቼሃለሁ" የሚል ድምጽ መስማቱንና ይህን ቀን ሲጠብቀው የነበረ በመሆኑ በርካቶች ማመንና መስማት ባይፈልጉም "ሙዚቃ በቃኝ" ብሎ ለመለየት መወሰኑን በአንድ ወቅት ከኢቢኤስ ቴሌቪዥን የ"እንጫወት" ፕሮግራም አዘጋጆች ጋር በነበረው ቆይታ ተናግሯል፡፡

ያለፉትን 37 ዓመታት መኖሪያውን በሀገረ አሜሪካ ቨርጂኒያ አድርጎ የቆየ ሲሆን፤ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ሳይመለስ ቆይቷል፡፡ ለረዥም ጊዜ በሕክምና ሲረዳ ቢቆይም፣ በተወለደ በ70 ዓመቱ ሚያዝያ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ሕይወቱ አልፏል፡፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱም ሚያዝያ 4 ቀን 2016 ዓ.ም የሕይወቱን ረዥም እድሜ በኖረባት አሜሪካ ተፈጽሟል፡፡ ለወዳጅ ዘመዶቹ እንዲሁም አድናቂዎቹ መጽናናትን በመመኘት አበቃን።

# ዓለም አቀፍ

## 100 ዓመት የደፈኑ የዕድሜ ባለፀጋዎች የሚጋሯቸው ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

100 ዓመት የደፈኑ የዕድሜ ባለፀጋዎች የሚጋሯቸው ሥነልቦናዊ ባሕሪያት አላቸው። አብዛኞቹ አሁንም ጤናማ ናቸው፤ ጥንካሬያቸው ያስቀናል፤ ከሰው ጋር ለማውራት ጉጉ ናቸው።

በእንግሊዝኛው ሴንቴናሪያንስ ይባላሉ። 100 ዓመት ያለፋቸው የዕድሜ ባለፀጋዎች ናቸው።

አብዛኞቹ ጭንቅላታቸው ሁሌም በእንቅስቃሴ እንዲጠመድ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ ስፖርት መሥራት አሊያም ጨዋታ መጫወት።

የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጥናት ክፍል እንደሚለው አሁን አሁን በርካታ ሰዎች የመቶ ዓመት ዕድሜያቸውን ለማክበር 100 ሻማ ሲለኩሱ መመልከት አዲስ ነገር አይደለም።

በአውሮፓውያኑ 1990 ይህን ፀጋ መጎናፀፍ የቻሉት 92 ሺህ ሰዎች ብቻ ነበሩ። በ2021 ይህ ቁጥር ወደ 621 ሺህ ተመንድጓል።

እርግጥ ይህ ቁጥር ለምን በዛ የሚለውን ለማወቅ ዘረ-መል እና የኑሮ ዘይቤን መመልከት ግድ ይለናል። ነገር ግን ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያትን መዘንጋት የለብንም።

ማሪያ ዶሎረስ ሜሪኖ በማድሪድ ኮምፕሉተንስ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልቦና ባለሙያ ናት። 100 ዓመት የደፈኑ የዕድሜ ባለፀጋዎችን ለዓመታት አጥንታለች።

ዘ ጆርናል ኦፍ ሀፒነስ ስተዲስ የተሰኘው መጽሔት ላይ በቅርቡ ባወጣችው አንድ ጥናት እነዚህ ሰዎች 19 ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያትን ይጋራሉ ትላለች።

ማሪያ እነዚህን ባህሪያት በስምንት ከፋፍላ እንዲህ ታቀርባቸዋለች።

እነኚህ የዕድሜ ባለፀጋዎች ከሚጋሯቸው ባህሪያት አንዱ ጥንካሬ ነው። ለመኖር ያላቸው



ጉጉት፣ ንቃታቸው እና ጉልበታቸው ከሌሎች ለየት ያደርጋቸዋል።

"በጣም የሚገርም ነው። ያናገርናቸው ሴንቴናሪያኖች የመኖር ፍላጎታቸው እጅግ ከፍ ያለ ነው" ስትል ማሪያ ዶሎረስ ሜሪኖ ለቢቢሲ ተናግራለች።

"ስታናግሪያቸው 100 ዓመት የደፈኑ አይመስሉም። በጠቅላላው በቃ በጣም ወጣት የሆነ ሰው የምትናጋሪ ነው የሚመስለው" ትላለች።

ማሪያ ለጥናቷ ካናገረቻቸው ሰዎች መካከል 98 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ሥራ ይሠሩ የነበሩ ወንዶች እና ሴቶች ይገኙበታል።

የዕድሜ ባለፀጋዎቹ ጭንቅላታቸውንም ሆነ አካላቸውን የሚያንቀሳቅስ ሥራ ከመሥራት አይቦዝኑም። በየቀኑ ደረጃ ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ፣ ካርታ ይጫወታሉ፣ ሱዱኩ የተሰኘው የቃላት ጨዋታንም ያዘወትራሉ።

ስቴሲ አንደርሰን የኒው ኢንግላንድ ሴንቴናሪያን ስተዲ ጥምር ዳይሬክተር ናት። ይህ መቀመጫውን በአሜሪካዋ ቦስተን ከተማ ያደረገ ማዕከል 100 ዓመት የደፈኑ የዕድሜ ባለፀጋዎችን ያጠናል።

ስቴሲ እነዚህን ሰዎች አንድ ከሚያደርጋቸው መለያ መካከል አንዱ ጥንካሬ መሆኑን ትስማማበታለች።

"አብዛኞቹ ሕይወትን በደንብ እንደሚያጣጥሙ ይናገራሉ። ይህ ለእኔ በጣም የሚደንቅ ነገር ነው" ብላለች ስቴሲ ለቢቢሲ።

በማሪያ ዶሎረስ ሜሪኖ ጥናት መሠረት ዕድሜያቸው ከ100 የተሻገረ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም ጤናማ ነው።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ሌላኛው 100 ዓመት የደፈኑ የዕድሜ ባለፀጋዎች የሚጋሩት ነገር ቁርጠኝነት ነው።

"በጠቅላላው ኃላፊነት የሚሰማቸው ናቸው። ተፎካካሪ እና ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው። ያሰቡትን ነገር ከማሳካት ወደኋላ አይሉም" የምትለው ማሪያ ናት።

በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፤ ክፍለ ዘመን የደፈኑ ሰዎች ከሚጋሯቸው ሥነ-ልቦናዊ ባህሪያት መካከል አንዱ ፅናት ነው።

ፅኑ መሆን ማለት ፈተናን መቻል ማለት ነው። እንዲያውም ይህን ልምድ ተጠቅሞ የበለጠ ጠንካራ መሆን ረዥም ዓመት ለመኖር መሠረታዊ ነው።

አጥኚዎች እንደሚሉት ከአንድ ክፍለ ዘመን ለላቀ ጊዜ እዚህች ምድር ላይ የኖሩ ሰዎች ውሳኔ ለመወሰን አይሳሱም፤ ሕይወታቸውን ተቆጣጥረው መኖር ይችላሉ።

በተጨማሪ አዲስ ነገር የማወቅ ጉጉት አላቸው። ትምህርት መገብየት ይወዳሉ። ራሳቸውን ያስተምራሉ።

"100 ዓመት ሞልቷቸው «እስካሁን ባልቆይ ደስ ይለኝ ነበር» የሚሉ ሰዎች ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ነገር ግን አንድ የ40 ዓመት ሰው እስከ 100 መኖር ትፈልጋለህ? ቢባል «አልፈልግም» እንደሚል እሙን ነው።"

እንደ አጥኚዎች ከሆነ እነዚህ ሰዎች ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ ምክንያታዊነት፣ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ማበጀት እና በፍጥነት መማር ይችላሉ።


## ማስታወቂያ

Enyi General Business PLC በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግስት ፣ አሶሳ ዞን፣ አሶሳ እና አብራሞ ወረዳዎች፣ ሸርቆሌ እና አፈንዳጎ በተባለው አካባቢዎች የወርቅ እና ቤዝ ሜታልስ ምርመራ ፈቃድ እንዲሰጠው መሥሪያ ቤታችንን ጠይቋል፡፡

**የጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔቶቹም፡-**

| Block Name | Comer Points | Easting | | | Northing | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Degree | Minute | Second | Degree | Minute | Second |
| Part 1 | 1 | 34 | 13 | 27.32 | 09 | 58 | 43.09 |
| | 2 | 34 | 16 | 29.48 | 09 | 59 | 0.67 |
| | 3 | 34 | 16 | 35.48 | 10 | 00 | 57.17 |
| | 4 | 34 | 13 | 37.04 | 09 | 59 | 52.47 |
| | 5 | 34 | 13 | 29.66 | 09 | 59 | 11.31 |

ስለዚህም የተጠየቀውን ፈቃድ ከመስጠታችን በፊት በተጠቀሰው አካባቢ በተለይም ከዚህ በላይ በተመለከቱት ጂኦግራፊክ ኮኦርዲኔቶች በሚከለል ቦታ ላይ ያገባኛል የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰባት/07/ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን በጽሑፍ ለመሥሪያ ቤታችን እንዲያቀርብ እናሳስባለን፡፡

**የማዕድን ሚኒስቴር**



## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ኢ/ክ/መ/በኮንሶ ዞን የካራት ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት በ2016 በጀት ዓመት ካራት ከተማ አስተዳደር የቄራ ግንባታ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ግንባታውን ለማስገንባት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የሥራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ባወጣው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገቢ ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 172/2011 በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተደራጁ ማህበራት/ድርጅቶችን አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**በዚህ መሠረት፡-**

1. በዘርፉ የ2015 ዓ/ም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው፡፡
2. በዘርፉ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው፡፡
3. በኮንስትራክሽን ዘርፍ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት ደረጃ GC-7 እና ከዚያ በታች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው እና ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ ሥር ያሉት በየትኛውም ክልል የመንግሥት ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች ጨረታ ጨረታ አሸንፈው የገቡት የውል ግዴታቸውን መፈፀም ያልቻሉ እና የተረከቡትን ሣይት ሣይጨርሱ ጥለው የወጡ እና የውል የማቋረጥ የተደረገባቸው ሥራ ተቋራጭ መወዳደር አይችሉም፡፡
4. በዘርፉ የአቅራቢነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው፡፡
5. በዘርፉ (Tin Number) የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ያላቸው፡፡
6. በ2015 ዓ.ም ግብር መከፈላቸው እና ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
7. በዘርፉ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ያላቸው፡፡
8. የዋጋ ማቅረቢያ በሚታይ ጹሑፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡
9. ተጫራቾች የጨረታ ሠነድ (Bill of Quantity) የማይመለስ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 21 /ሃያ አንድ/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ኮንሶ ዞን ካራት ከተማ አስተዳደር ገቢዎች/ባ/ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ በመክፈል ኮንሶ ዞን ካ/ከ/አስ/ር/ፋ/ጽ/ቤት ግዥና ን/አስ/ር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር -4 በመቅረብ ሠነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
10. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያውን ሰነድ ፋይናንሻል ኦርጅናል 1 ፋይናንሻል ኮፒ 1 እና ኮፒ 2 እንዲሁም ቴክኒካል ኦርጅናል 1 ቴክኒካል ኮፒ 1 እና ኮፒ 2 ለየብቻ ለይቶ በስድስት ፖስታ በማድረግ በአንድ በታሸገ እናት ፖስታ ውስጥ አድርገው በላዩ ላይ የድርጅቱን ህጋዊ ማህተም፣ አድራሻ፣ ስምና ፊርማ በማሳረፍ በ22ኛው የሥራ ቀን ካ/ከ/አስ/ር ፋ/ኢ/ጽ/ቤት በአካል በመገኘት ለጨረታ የተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
11. ዕጩ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ከሞሉት ጠቅላላ ዋጋ 0.5% /ዜሮ ነጥብ አምስት ፐርሰንት/ በጥሬ ገንዘብ ወይም ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ የተረጋገጠ ቼክ፣ CPO ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተርኦፍ ክሬዲት ከቴክኒካል ኦርጅናል መረጃዎች ጋር በፖስታ አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
12. የጨረታው ሳጥን የሚታሸገው በ22ተኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን የሚከፈተው በዚሁ ዕለት ልክ ከረፋዱ 4፡30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
13. ጨረታው ይከፈታል በተባለበት በ22ኛው ቀን በመንግሥት የሥራ ቀን ላይ ካልዋለ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
14. ሌሌች ተጫራቾች በሚያቀርቡት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡
15. አሸናፊው ድርጅት የውል ማስከበሪያ ሰነድ 10% እና ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ይዘው ቀርበው ውል ባይገቡ በዘርፉ ለጨረታ ማስከሪያ ያስያዙት ገንዘብ ለመንግሥት ውርስ ሆኖ ጨረታው ይሰረዛል፡፡
16. በጨረታ መክፈቻ ዕለት ተጫራቾች ተሟልተው ያለመገኘት የጨረታውን አከፋፈት ስነ-ሥርዓትን ሊያስተጓጉል አይችልም፡፡
17. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 09-00-69-71–33/09-20-98-00-30/09-23-36-80-85**

**ደውለው ያግኙን**

**በኮንሶ ዞን የካራት ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

**ካራት**

# ስፖርት





## ካንሰርን ያሸነፈችው ኮሎምቢያዊት ኮከብ!

ቦጋለ አበበ

34ኛውን የአፍሪካ ዋንጫን አዘጋጇ ኮትዲቯ ድራማዊ በሆነ ክስተት ራሷ አስቀርታለች። ብሔራዊ ቡድኑ ዋንጫ ከማንሳቱም በላይ ከካንሰር ሕመም አገግሞ ሀገሩን ለቻምፒዮንነት ያበቃው ሴባስቲያን ሀለር ጉዳይ አነጋጋሪ ሆኖ ነበር። ለጀርመኑ ክለብ ቦሩሲያ ዶርትመንድ የሚጫወተው ሀለር፣ ለስድስት ወራት ሲሰቃይበት ከነበረው የወንድ የዘር ፍሬ ካንሰር ህመም ታግሎ በማሸነፍ ነበር ሀገሩን ለዚህ ክብር ማብቃት የቻለው።

እንደ ሀለር ከባዱን ፣ ተስፋ አስቆራጩንና አስፈሪውን የካንሰር ህመም በታላቅ ጽናት ታግለው በማሸነፍ ስኬታማ መሆን የቻሉ ጥቂቶች ናቸው። የሴቶች እግር ኳስ ዓለም ዋንጫ ኮከቧ ሊንዳ ካይሴዶ ከጥቂቶቹ አንዷ ናት። የኮሎምቢያ የሴቶች እግር ኳስ ምልክት የሆነችው ሊንዳ ልክ እንደ ሀለር ካንሰርን ታግላ ያሸነፈች የጽናት ምሳሌ ናት።

ሊንዳ ካይሴዶ የተወለደችው በደቡብ አሜሪካዊቷ ኮሎምቢያ ካንደሊሪያ ነው። ቤተሰቦቿም ይህ ነው የሚባል ገቢ አልነበራቸውም። ልጅነቷንም ያሳለፈችው በድህነት ነው። የእግር ኳስ ኮከቧ አሁንም የመጣችበትን አልረሳችም። በቅርቡም ወደ ትውልድ መንደሯ አቅንታ ለበርካቶች ምግብ እና የሚያስፈልጋቸውን ቁሶች ይዛ ሄዳለች። ይህንን በጎ ነገር ስታከናውንም ሚዲያ እንዲኖር አልፈቀደችም።

ወጣቷ የእግር ኳስ ኮከብ ሊንዳ የፕሮፌሽናል እግር ኳስ ሕይወትን የተቀላቀለችው ገና በ14 ዓመቷ ነበር። እአአ በ2019 የኮሎምቢያው ክለብ አሜሪካ ደ ካሊን ተቀላቀለች። በዚሁ ዓመት ኅዳር ወር ላይ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ጥሪ ደረሳት። ሆኖም ይህ ትልቅ እድል ሆዷ ላይ በሚሰማት ህመም ተገታ። በ2020 የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዓለምን እየረበሻት በነበረበት ወቅት፣ እሷም ህመሟ እየጠና ሄደ። ሊንዳ የህክምና ምርመራ ስታደርግ የእንቁላል ማከማቻ ካንሰር (Ovarian cancer) እንዳለባት ተነገራት።



ከምርመራው ሁለት ሳምንታት በኋላ ዕጢ ለማስወገድ ቀዶ ህክምና ያደረገችው ሊንዳ፤ አንደኛው የእንቁላል ማከማቻ (አቫሪ) እንዲወገድ ተደረገ። የሞት ትኬት ተቆርጦላት የነበረችው ሊንዳ፤ ከካንሰር ህመሟ ማገገም ቻለች። ለዚህም ቤተሰቧ እና የኮሎምቢያ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ኔልሰን አባዲ ያደረጉላትን ድጋፍ እንደረዳት ትናገራለች።

“አስቸጋሪ ወቅት ነበር። ፈጣሪ ይመስገን፣ በብዙ ትግል ፈተናውን ተቋቁሜ ማለፍ ችያለሁ” የምትለው ሊንዳ በዚያ የፈተና ጊዜ ውስጥ ቤተሰቦቿ ሁሌም ከጎኗ ነበሩ። የአሰልጣኟ አብሮነትም አልተለያትም ነበር። “ አሰልጣኜ በርካታ ጊዜ ይደውልልኝ ነበር። አንድ ቀን ቀዶ ህክምና እየሄድኩ በጣም ከፋኝ። ከዚህ በኋላ በደንብ እግር ኳስ መጫወት እንደማልችል ተሰማኝ። እሱም ዘና በይ፤ አይዞሽ ትመለሻለሽ ሲል አበረታኝ። የተስፋ ስንቅ ሆነኝ። በዚህ መልኩ ከነበርኩበት እጅግ በጣም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ በአሸናፊነት ወጣሁ። በታላቁ የዓለም ዋንጫ መድረክም ለመጫወት በቃሁ” ስትል በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ በማለፍ ለስኬት እንደበቃች ታስታውሳለች።

ሊንዳ ከቀዶ ህክምናዋ በኋላ ለስድስት ወራት የኬሞቴራፒ (የካንሰር የጨረር ህክምና) አድርጋለች። ህክምናዋን ከጨረሰች ከቀናት በኋላም ከካንሰር ነፃ መሆኗ ተነገራት። ከዚያም ወደምትወደው የእግር ኳስ ሕይወት ለመመለስ እንደቻለች ገልፃለች። በኋላም ዲፖርቲቮ ካሊ ከተሰኘው የእግር ኳስ ክለብ እና በብሔራዊ ቡድኑ መጫወትን ቀጠለች። ሊንዳ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎች ተሳትፋለች። በ2022 በሚያስደንቅ ሁኔታ በደቡብ አሜሪካ ከ17 ዓመት በታች የሴቶች ሻምፒዮና፣ በኮስታሪካ ከ20 ዓመታች የሴቶች የዓለም ዋንጫ፣ በሕንድ ከ17 ዓመት በታች የሴቶች የዓለም ዋንጫ እና ኮፓ አሜሪካ ፌሚኒና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተጫውታለች ።

በነዚህ ውድድሮች ዓለም ስለ ሊንዳ ድንቅ ችሎታ ለመረዳት ችሏል። በወቅቱ የኮፓ አሜሪካ አዘጋጅ የነበረችው ኮሎምቢያን ለፍጻሜ ስትደርስ የ17 ዓመቷ ሊንዳ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች ሆና ተመርጣለች። መንፈሰ ጠንካራዋ ሊንዳ በ2023 የሴቶች የዓለም ዋንጫ ሀገሯን ኮሎምቢያን ወክላ በታላቁ መድረክ አንፀባርቃለች። የ19 ዓመቷ ሊንዳ በመድረኩ ግብ ያስቆጠረች ሲሆን፤ በዚህም በዓለም ዋንጫ ውድድር ታሪክ በትንሽ ዕድሜዋ ጎል ያስቆጠረች ሁለተኛዋ ደቡብ አሜሪካዊት ተጫዋች ሆናለች።

ሊንዳ በአሁኑ ወቅት በዓለም ምርጥ ከተባሉት ክለቦች አንዱ ለሆነው ሪያል ማድሪድ እየተጫወተች ትገኛለች። በኮሎምቢያው የዓለም ዋንጫ ቡድን ውስጥ ለስፔን ክለቦች ከሚጫወቱ ሰባት እግር ኳስ ተጫዋቾች መካከል ተጠቃሽ ሆናለች። በማድሪድ ጥሩ ጊዜን እያሳለፈች ያለችው ሊንዳ፤ “አሁንም በጣም ወጣት ነኝ። አሁንም ብዙ መማር አለብኝ። በዚህ ቡድን ውስጥ በየቀኑ ልምድ አገኛለሁ። ይህ የመጀመሪያዬ የዓለም ዋንጫ ነው። በዚህም መደሰት እፈልጋለሁ። ብዙ ጊዜ አለኝ” ስትል በታዳጊነቷ ትልቅ ፈተና ተጋፍጣ ያለፈችው ኮከብ በቀጣይ ብዙ ሥራ እንደሚጠብቃት ተናግራለች።


## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ-የኢ/ገ/ሚ/ምዕ/ አ/አ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት/ምዕ-2016/04

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ከመንግስት በተመደበለት በጀት የተለያዩ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን በሎት በመደልደል በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሎት ቁጥር | የዕቃው ወይም አገልግሎቱ ዓይነት |
|---|---|---|
| 1. | ሎት-1 | የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች |
| 2. | ሎት-2 | የባለ አራት ኮከብ ሆቴል አገልግሎት |
| 3. | ሎት-3 | የተለያዩ የህትመት አገልግሎቶች |
| 4. | ሎት-4 | ለሰራተኞች የሚሆን የታሸገ የመጠጥ ውሃ 0.6ሚ.ሊ ወይም ግማሽ ሊትር |

**በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡**

1ኛ.በዘርፉ የንግድ ምዝገባ ፍቃድ ፡፡

2ኛ.በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፍቃድ፡፡

3ኛ.የግብር ከፋይነት ሰርተፍኬት፡፡

4ኛ.የቫት ተመዝጋቢነት ሰርተፍኬት፡፡

5ኛ.በጨረታ መሳትፍ እንደምትችሉ የሚገልፅ ግብር የተከፈለበት ክሊራንስ ፡፡

6ኛ.ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረገፅ ላይ በአቅራቢነት ስለመመዝገቡ መረጃ በማያያዝ ማቅረብ የምትችሉ፡፡

7ኛ.ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን በC.P.O (ሲ.ፒ.ኦ) ወይም በBid Bond ከሚያቀርቡት (ከሚወዳደሩበት) ጠቅላላ ዋጋ ለእያንዳንዱ ሎት 1% (አንድ በመቶ) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

8ኛ.ተጫራቾች በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ተቋማት ከሆኑ ካደራጃቸው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

9ኛ.ተጫራቾች ለጨረታ ሰነድ (ለእያንዳንዱ ሎት) ብር አንድ መቶ (100.00) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 (አስራ አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት በመስሪያ ቤቱ ህንፃ ወለል (ፍሎር) 5ኛ ፎቅ ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር የስራ ሂደት ቢሮ በአካል በመምጣት የጨረታ ሰነድ መግዛት ይችላሉ፡፡

10ኛ.ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16 ኛው የስራ ቀን በታሸገ ፖስታ ፋይናንሻል ኦርጂናል እና ኮፒ፤ ቴክኒካል ሰነድ ኦርጂናል እና ኮፒ ለየብቻ የድርጅቶቻቸውን ማህተም በማድረግ ለጨረታ ማስገቢያ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ 3፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት አለባቸው፡፡ ጨረታው ተጫራቾች በተገኙበት ወይም ባይገኙም በዚያኑ እለት በ 3፡15 ሰዓት ታሽጎ በ3፡30 ሰዓት 5ኛ ፎቅ ይከፈታል፡፡

11ኛ.ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 (አስራ አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት ቅዳሜን ጨምሮ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

12ኛ.ተጫራቾች ላሸነፉበት እቃ በግዥ መመሪያ መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች የግዥ ትዕዛዙን ውል ከመፈረሙ በፊት ምንም ዓይነት የዋጋ ለውጥ ሳይደረግ 20% ክፍ ወይም ዝቅም ብሎ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

13ኛ. ተጫራቾች አሸናፊ ሆነው ለተገኙበት ዕቃ ከአጠቃላይ ዋጋው 10% የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

14ኛ.ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ** ፡-የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግሎባል ሆቴል አጠገብ የቀድሞ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 5ኛ ፎቅ ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር የስራ ሂደት ቢሮ፡፡

**ስልክ ቁጥር፡- 011-5-54-17-58 ወይም 011-5-53-06-65**

**የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር**




# ልጆች እንዲያብቡ ያንብቡ

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ? ልጆችዬ ትምህርት እና ጥናት እንዴት ነው? በርትታችሁ እየተማራችሁ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ልጆች መቼም ከትምህርት ጋር የተያያዘም ሆነ ከትምህርት ውጭ ያሉ እውቀቶችን ለማግኘት ንባብ አንዱ መሳሪያ መሆኑን ትረዳላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ታዲያ ሳምንት በገባነው ቃል መሠረት ዛሬ ስለ ልጆች የንባብ ባሕል የምንላችሁ ይኖረናል፡፡ ከእናንተ የሚጠበቀው ታዲያ ትኩረት ሰጥታችሁ ማንበብ ብቻ ነው። ወይም ወላጆቻችሁ የሚያነቡላችሁ ከሆነ እነርሱን በጥሞና ብትከታተሉ መልዕክቱን ለመረዳት በሚገባ ያግዛችኋል፡፡

የልጆች የንባብ ባህል እንዲያድግ፣ እንዲስፋፋ እና እንዲጎለብት ከሚሠሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል ‹‹ኢትዮጵያን ሪድስ›› አንዱ ነው፡፡ ድርጅቱ አራተኛው ዓመታዊ የሕፃናት ንባብ ጉባኤን ‹‹በቅደመ መደበኛ ትምህርት ልጆችን በንባብ መደገፍ›› በሚል መሪ ሃሳብ ሚያዝያ 3 እና ሚያዝያ 4 ቀን 2016 ዓ.ም አካሂዷል፡፡

በዚህ መድረክ ላይ አንጋፋ የሚባሉ ደራሲዎች፣ የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከተለያዩ ቦታ የመጡ እንግዶች የእናንተን የንባብ ባህል ለማሳደግ በጥቅሉ ‹‹ምን ይሠራ? በማለት ውይይት አድርገዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ውይይት መደረጉ ደስ ይላል አይደል? ‹‹አዎ፡፡›› ምክንያቱም እናንተ አንብባችሁ ተመራማሪ፣ ጠያቂ፣ አስተዋይ እና የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች እንድትሆኑ ለማገዝ ያለመ ነውና፡፡

ሌላው በዚህ ጉባኤ የ‹‹አምባ ትምህርት ለተቸገሩ በጎ አድራጎት ማሕበር›› ተማሪዎች ለታዳሚዎች የሚከተሉትን መዝሙር አቅርበዋል፡፡

**አንቺ እማማ ኢትዮጵያ የእኔ የእኔ፣**
**እኔም የአንቺ አንቺም ለእኔ፡፡**
**ርሃብ ጥማቴን አትውጂም አንቺ ፣**



**ክፋቴን ሲባባ አንጀቴ፡፡**
**ነፃነት ብርሃን ብሩህ ወጋገንሽ፣**
**አንድነት ሁሌም ይኖር ለዘላለም፣**
**እናት ዓለም፡፡**
**ኢትዮጵያ አንቺ ካለሽ ሁሉ ለእኔ፣**
**ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የእኔ፡፡**

ልጆችዬ መዝሙሩን ወደዳችሁት? ስለ ኢትዮጵያ በጋራ ሲያዜሙ ብትመለከቷቸው ደግሞ በጣም ደስ ይላሉ፡፡ ሌላኛውን መዝሙራቸውን እናስነብባችሁ አይደል?

*መተኪያ ለሌላት ፣*
*እስኪ ልዝፈልንላት፣*
*እማምዬ እንበላት፡፡*
*ዘወትር ትኩሳቴን ፣*
*ለምታዳምጠው፣*
*ለእማምዬ ልዝፈን ፣*
*ለማትለወጠው፡፡*
*ፊቴ ተኮሳትሮ ማየት መች ትሻለች፣*

**ስደሰት በመሳቅ ሳዝን ትከፋለች፡፡**
**ሁሉ ልጅ ለእናቱ ገና ልጅ ነውና ፣**
**እናቱን የማይወድ ምን ፍጡር አለና?**
**መተኪያ ለሌላት ፣**
**እስኪ ልዝፈልንላት፣**
**እማምዬ እንበላት፡፡**
**በማለት ዘምረዋል፡፡**

በጉባኤው ከውይይቶች በተጨማሪ የልጆች መጻሕፍት አውደ ርዕይ ተካሂዷል፡፡ በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በጉራጌኛ፣ በትግርኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በእንግሊዝኛ እና በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ የተረት እንዲሁም ልጆችን ያስተምራሉ ተብለው የተጻፉ መጻሕፍት ቀርበዋል፡፡

በጉባኤው የተገኙት አቶ መዝገቡ ባያዝን የትምህርት ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። እርሳቸው እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ‹‹ኢትዮጵያ ሪድስ››ን ጨምሮ በሕፃናት ንባብ እድገት ላይ ከሚሠሩት ጋር በጋራ ለመሥራት ፍላጎት አለን ብለዋል፡፡ የሕፃናት የንባብ ባህል ለማሳደግ የንባብ ቦታዎችን እንዲሁም ሁኔታዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡ ሕፃናቱ በአቅራቢያቸው ቤተ መጻሕፍት እንዲገነባ እና መሰል ሥራዎችን መሥራት የሁለም ኃላፊነት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት (ወመዘክር) ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ይኩኖ አምላክ ይባላሉ፡፡ ተረት ተረት ለታዳሚዎች በማቅረብ ልጆች ከተረት ብዙ ነገሮችን መማር እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ‹‹ኢትዮጵያ ሪድስ›› የልጆች ንባብ እንዲያድግ እየሠራ ያለውን ተግባር በማመስገን ከሁሉም የበለጠ መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ልጆችዬ! በአጠቃላይ በጉባኤው የሕፃናት የልጆች የንባብ ባሕልን ለማሳደግ ‹‹ኑ በጋራ እንሥራ›› የሚል መልዕክት ተላልፏል፡፡

እንደ ‹‹ኢትዮጵያ ሪድስ›› ያሉ ድርጅቶች፣ በግለሰብ፣ በመንግሥት፣ በልጆች መጻሕፍት ፀሐፊዎች እንዲሁም ወላጆቻችሁ እናንተ አንብባችሁ እውቀት እንድትሸምቱ ጥረት እንደሚያደርጉ ተገንዝባችኋልን ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ታዲያ እናንተስ የንባብ ክህሎታችሁን ለማዳበር ምን ጥረት እያደረጋችሁ ነው? ከትምህርት እና ከጥናት የተረፋችሁን ጊዜ በንባብ እያሳለፋችሁ ነው? ወላጆቻችሁ ወደ ቤተ መጻሕፍት እንዲወስዷችሁ ትጠይቃላችሁ? በዚህ አጋጣሚ ያገኛችሁትን አጋጣሚ በመጠቀም የምታነቡ ልጆች በጣም ጎበዞች መሆናችሁን መግለጽ እንፈልጋለን፡፡ በዚሁ ቀጥሉበት ማለትም እንወዳለን፡፡ የንባብ ልምምድ ያልጀመራችሁ ወይም ገና የሆናችሁ ልጆች አትጨነቁ ግን ቶሎ ጀምሩ ነው የምንላችሁ፡፡

በሉ ልጆችዬ ለዛሬው በዚሁ እናብቃ አይደል? በሰላምታ እንደጀመርን ሰላም በመመኘት መሰነባበት ተገቢ ነው፡፡ እናም ልጆች መልካም የትምህርት፣ የጥናት እና የንባብ ጊዜ እንዲሆንላችሁ ተመኘን!